# ትግላችን

አለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር

ወርሃዊ መፅሄት

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የተዘጋጀ

## የማህበረት ችግር

ክፍል ሁ ለ ት

የመፅሄት አዘጋጅ ቦርድ፣
P.O.BOX 3198
103 64 STOCKHOLM 3
SWEDEN

ቁጥር **3**

መጋቢት 1965

# መግቢያ

ባለፈው የትግላችን ቁጥር/ቁጥር 3.ጥር–የካቲት 1965/ ስለማህበሮች ችግር አንድ ረዥም ጽሁፍ ቀርቦ አንደነበረ ይታወሳል።ይህ ጽሁፍ ያልጄሪያ ጓዶች ለ12ኛው የአውሮፓ ማህበራችን ጉባኤ ያቀረቡት ነበር።ይህ በዚሁ በተባለው መጽሄት መግቢያ ላይ ተጠቅሷል።

ይኸው አሁን ደግሞ በዚህኛው የትግላችን ቁጥር ላልጀሪያ ጓዶች ጽሁፍ መልስ እንዲሆን ከአንድ አባል የቀረበለን ጽሁፍ እናወጣለን።ጽሁፍ ከተላከልን ቆይቷል። ይህን ከጽሁፎቹ አንዳንድ አባባሎች ለመረዳት ይቻላል።

ጊዜ ከማጠሩ የተነሳ ጽሁፉ እስከዛሬ ሳይወጣ መቀረቱ ስህተት መሆኑ ይሰማናል።ከዚህም በላይ በጥድፊያ በመሰራቱ አንዳንድ ቦታ ላይ አንባቢያችን ትንሽ ባያስቸግር አይቀርም።ድርብና መጪት ስለሚበዛው።ለሁለቱም ጉድለቶቻችን አንባቢያችን በቅድሚያ ይቅርታ እንጠይቃለን።

ትግላችን

## ያልጄሪያ ጓዶች ለ12ኛው ያውሮፓ ማህበር ጉባዔ 'ያቀረቡት ጥናት'

እንደሚታወሰው የ12ኛው ያውሮፓ ማህበር ጠቅላላ ጉባዔ አርእስት 'ሕዝባዊ ዲሞክራሲና የድርጅት ጥያቄ በኢትዮጵያ' የሚል ነበር:: በጉባዔው ላይ የነበሩ ጓዶች ሁሉ እንደሚያስታውሱት በዚህ አርእስት ላይ ከሁለት ቅርንጫፍ ማህበራት በተራ ጥናቶች ቀርበው ለየኮሚሽኖች ታድለው ነበር:: አንዱን ጥናት ያቀረበው ማህበር የሶቪየት ሕብረት ነበር:: እንዲያውም እኔ ያየኋቸው የሶቪየት ሕብረት ጥናቶች ሦስት ነበሩ:: "ብሔራዊ ዲሞክራቲክ ረቮሉሽንና የድርጅት ጥያቄ በኢትዮጵያ"፣ "የረጅም ጊዜ ሕዝባዊ ጦርነት" "የደረጠ ውጊያ":: ሁለተኛው ማህበር የስዊድን ሲሆን የጥናቱም አርእስት "ሕዝባዊ ዲሞክራሲና ድርጅታዊ ጥያቄ" የሚል ነበር:: እነዚህ ጥናቶች በኮሚሽኖች ሁሉ ውስጥ ታድለው ተነበው ነበር::

አሁን ጉባዔው ካለፈ በአራት ወራት በኋላ ያልጄሪያው ማህበር ለጉባዔው "አቀርቤት" የነበረውን የ54 ገጾች ጽሁፍ እንዳጋጣሚ አንድ ጓድ ጋ አገኘሁት:: ይህንን ጽሁፍ ፈጽሞ በስብሰባው ላይ አላየሁትም ነበር:: የቀሩትም የስብሰባው ተካፋዮች ጽሁፉን ማግኘታቸውን እጠራጠራለሁ:: በነገሩ አንዳች ያልተበረረ ነገር አለበት:: ወይ ያውሮፓው

ማህበር ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ፣ ጽሁፉን በጊዜ አላገኘትም፡ በስብሰባው ላይ ባያሠራጨው ቀርቷል ማለት ነው:: ይህ ከሆነ ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴው ትልቅ ጥፋት አድርጓል፣ መወቀስ አለበት:: ወይንም ያልጀሪያ ጓዶች ጽሁፉን ለሥራ አስኪያጅ ኮሚቴው ፣ ወይም ለጉባዔው ፣ ባይልኩ ቆይተው አሁን በየቦታው ለተመረጡ ሰዎች አሠራጭተውታል ማለት ነው:: ይህ ከሆነ ፣ ይህ ፀረ-ድርጅት ድርጊት መኮነን አለበት:: ለማንኛውም ጉዳዩን ሁለቱ ወገኖች — የቀድሞው ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴና ያልጀሪያ ማህበር— ማብራራት አለባቸው::

ያልጀሪያው ማህበር ጥናት ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ጥናቶች ይለያል:: ጓዶች ጥናቱን ያቀረቡት በሁለት ክፍል ነው:: ክፍል-አንድ "በኢትዮጵያ የሚመሠረው ሕዝባዊ ዲሞክራሲና የአብዮታዊ ድርጅት ጥያቄ፣ ከገጽ 1 እስከ 26 ፣ ክፍል-ሁለት "በኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራት ውስጥ ስለተነሣው ችግር" ፣ ከገጽ 27 እስከ 54:: (ጽሁፉ በእጅ ተጽፎ በፎቶ ኮፒ የተባዛ ነው:: ገጾችን የምጠቅሰው ከርሱ ነው::) በመጀመሪያው ክፍል ውስጥ ስለኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ፣ በተለይም ስለፊውዳላዊ ሥርዓት አስተዳደርና ልዩ ጠበቆች፣ ስለጊዜያዊው ሁኔታው ፣ ስለብሄራዊ ጭቆና፣ ስለኢምፔሪያሊዝም፣ ስለመሠረታዊ ቅራኔዎች ፣ ስለኢትዮጵያ ሬቮሉሽን ከጻፉ በኋላ፣ የእርእስቱን ሁለተኛ ክፍል የሚመለከተውን — የድርጅቱን ጥያቄ — በግማሽ ገጽ ሸኝተውታል:: ስለዚያውም ፣ "በዚህ እርእስ ውስጥ(" የአብዮታዊ ሀይልና



የድርጅት ጥያቄ" የሚለው እርእስት-ውስጥ ማለት ነው)በተጠቀሱት ሀሳቦች ላይ በተለይ አስተያየት ለመስጠት የምፈልገው "ድርጅታዊ ግዴታ" በሚለው ሀሳብ ላይ ነው::" ይሉና የተባለውን __አስተያየታቸውን__ በአምስት ጥያቄዎች መልክ አቅርበው ጉባዔው በነዚህ ጥያቄዎች ላይ እንዲወያይ ይጠይቃሉ:: አስተያየትን በጥያቄ መልክ ለማቅረብ ይቻላል ቢባልም፣ እንደውነቱ ከሆነ ስለእርእስቱ ሁለተኛ ግማሽ ከጓዶች የቀረበ ግልጽ አስተያየት የለም:: ለዚህ ለእርእስቱ ሁለተኛ-ክፍል ጓዶች ተገቢውን ቦታ አልሰጡትም:: በተለይም የተማሪ ማህበራት ተግባር ምን እንደሆነ በሰፊው "አስተያየት" ለመስጠት ቢችሉ ይህንን አላደረጉትም::

የጽሁፉ ክፍል-አንድ ብዙ አከራካሪ ነጥቦችን ይዘአል:: ለምሳሌ የኢትዮጵያ ፊውዳሊዝም ልዩ "ጠባዮች"፣ በኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ውስጥ ስላሉት መሠረታዊ ቅራኔዎች፣ ስለመደቦች ፣ ወዘተ በተሰነዘሩት ትንተናዎች ላይ ያሉኝን ሂሶች በቅርብ ደስ ባለኝ ነበር:: ምናልባት ጊዜና ሁኔታ ከፈቀደ እመለስበቸዋለሁ:: በዚህ ጽሁፍ ውስጥ፣ ከነዚህ ጥያቄዎች ይበልጥ አስቸኳይ መስሎ የሚታየኝን፣ ሁለተኛውን ክፍል ለመመልከት እፈልጋለሁ:: የሁለተኛው ክፍል ይበልጡ የተጻፈው __ያውሮፓውን ማህበር አመራር ለመንቀፍ ፣ በጠቀሳሳው በውጭ አገር ያሉትን ማህበሮቻችንን የቀደሞ መሪዎች ለማስጠቃትና ያልጄሪያን ጓዶች ትክክለኛነት__ ፣ "__ንጽሕ"ረቨቅኛናዊነት ወዘተ በዚሁ አማካይነት ብቻ አድርጎ ለማሳየት መሆኑ ከመላ ጽሁፉ ግልጽ ነው::__ በኔ አስተያየት

የዚህ ዓይነት አሠራር ለተማሪ ማህበሮቻችን ብቻ ሳይሆን ጓዶች መላለባው ለሚያነሡት የኢትዮጵያ ተራማጅ ሀይል አደገኛ ነው:: ይከፋፍላል፣ እርስ በርስ ያጋጫል:: ይህም በተጨበጠ አኳኋን (ኦብጄክቲቭሊ) ለኢትዮጵያ አድሃሪ ሥርዓት ዐርዳታ ይሆናል::

ጓዶች በጽሁፋቸው መጨረሻ ላይ እንዲህ ይላሉ "መልስታችንን የጻፍነው በንጹሕና በቅን መንፈስ፣ ከልብ የተሰማንን ልክ እንደተሰማን (ሳንሸፍን) ነውና ጉባዔውና ተወቀስን ብለው የሚያምኑ ጓዶች መልስታችንን በቅን መንፈስና በረቮሉሽነሪ ዴሞክረት እንዲቀበሉልን እንጠይቃለን:: ሂስ በቀረበባቸው ጉዳዮች ላይ የተለየ አስተያየት ያላቸው ሰዎች ከላይ በጻፍነው ጽሁፍ ወይም በሌላ ጊዜ በይፋ በገለጽነው ወይም በስማችን በወጣነው ጽሁፍ ላይ የተመሠረተ፣ በግልጽ ቋንቋና በይፋ የሚቀርብ ሂስ እንጂ "እውነተኛ ዓላማቸው"፣ "እነርሱ የሚፈልጉት"፣ "እነርሱ የሚሉት" እየተባለ በሚነዛበት ወሬ ላይ የተመሠረተ አሽሙርና ውስጠ ወይራ የተሞላበት ዘለፋ እንዳይሰነዘርብን አደራ እንላለን:: አስተሳሰባችንን በመሰላቸው ተርጉመው ሰዎች ለሚሰጡን ፖለቲካዊ ስያሜ (ፔቲቡርዧ ናሽናሊስት፣ አናርኪስት፣ ሶሽል ሸቪኒስት ወዘተ) ዘቶ ግድ የለንም፣ ያበረታታናል፣ የተሳሳተ መሆናቸውን እናስረዳለን ወይንም አረባችንን



እናስወጣለን:: በስለላና በአድሃሪ ፕሮፓጋንዳ ተገፋፍተው "ጓዶች" ለሚሰነዝሩብን ተንኮል፣ የፈጥጣል አሽሙርና ውስጠ ወይራ ሳለበት "ሂስ" ጠርሰ ትዕግሥት የለንም፣ ይዘገንነናል፣ ግን ዎን እናደርጋለን፣ ሥራቸው እስኪያጋልጣቸው እንጠብቃለን::" (የመጨረሻው ምርዝ የተጠመረ)

መችስ ጓዶች ሥራቸውን 'ንጹሕ፣ ቅን ወዘተ' ብሳሉት በርግጥም እንደርሱ ናቸው አይባልም :: ደግሞም የጽሁፋቸውን ገብዝነትና ጉረኛነት በደንብ የተመለከተ ማንኛውም ሰው ሊገምተው እንደሚችለው፣ አረባቸው "መለወጣቸው" ፈጽሞ የሚሆን ነገር አይመስልም:: ለዚህ ነው ይህንን ጽሁፍ ለማቅረብ የተነሣሁት::

ይሁንናም፣ ይህ የጽሁፋቸው መጉጊያ አንቀጽ ከላይ ያልሁትን የጽሁፋቸውን ዋና ዓላማ በደንብ ቁልጭ አድርጎ ያሳያል:: ያልጀሪያ ጓዶች ሐቀኞች፣ በቅን መንፈስ፣ በንጹሕ መንፈስ፣ "ሂስ" አቅርበዋል:: "ሂሱን" ያቀረቡት በስላዮችና በአድሃሪዎች ተገፋፍተው በነዚህ ጓዶች ላይ ተንኮል በሚሰነዝሩ "ጓዶች" ላይ ነው:: ከዚህ በታች እንደምናየው ይህ "ሂስ" የሚመለከተው በጠቅላላው በውጭ አገር ማህበሮቻችን አመራር ውስጥ የነበሩትንና ያሉትን ሰዎች ነው:: ከነዚህ የሚፈለገው ከልጀሪያ ጓዶች የቀረቡትን "ሂሶች" "በቅን መንፈስና በረቮሉሽናሪ ዴሞክራት" በመቀበል የጓዶችን ትክክለኛነት፣ ሀቀኛነት ወዘተ ማጽደቅ ነው! ግን ይህ ብቻ አይደለም:: "ሂሱን" ያቀረቡባቸው ሰዎች "በዚህ ጉባዔ አጻፈሽ ቢሉና ያስወሩትን የሚያምኑበትና እውነት ነው፣ ወይንም መቶኛ ዓላማ የ

ለበትም የሚሉ ከሆነ ፣ ይነሡና ይደገፉት:: አለዚያ የጉባዔ
ው ተካፋዮች እንደነዚህ ዓይነቶች ሰዎች ሲያጋጥሟቸው ሰላይ
ወይም የፊውዳል ገዥዎች መሣሪያ ብለው እንዲሰይሙልን እንጠይ
ቃለን::"(ገጽ 37) ይህ መቻስ በኔ አስተያየት የጉረኛነት መ
ጨረሻ ነው:: ግን ከዚህ በላይ በጠቀስሁት ጥቅስ በራሱ ውስጥ
ና ከዚህኛውም ጋር ያለውን ተቃርኖ አንባቢ ያስተውል:: ባን
ዱ በኩል ሰዎች ለሚሰጧቸው የፖለቲካ ስያሜ ከቶ ግድ የላቸው
ም ፣ ያበረታታቸዋል ፣ በሌላ በኩል ግን የሚሰነዘርባቸው ተ
ንኮል ትዕግሥታቸውን ይጨርሰዋል ወዘተ ፣ ይሁንናም አዳማጭ ፣
አንባቢ ፣ በነርሱ ፈንታ እንዲሰደበላቸው ይጠይቃሉ:: ሕይወ
ቶን እንዲጥላቸው አለመጠየቃቸው አስገርሞኛል! አሥራሁለተኛ
ው ጉባዔ የቀረበለትን ጥናት ትቶ ስለነዚህ ጓዶች ብቻ እንዲ
ያወራ አለመጠየቃቸውም ገርሞኛል!

ጓዶች "እውነተኛ ዓላማቸው" እንደዚህ ነው ብለው
አይተርጉሙብን ይላሉ:: እነርሱ ግን የሌላውን አስበ ተርጉመ
ው ዓላማውን ሊያወጡ መብት አላቸው:: እንደሚሉት ከሆነ
ወሬ በነርሱ ላይ ተነዝቷል ፣ "ወሬው የተነዛው ለተወሰነ
ዓላማ ነው፣ በተማሪው ሕሊና ውስጥ ባለው የፊውዳል አስተሳሰ
ብ በመጠቀም በእኛ ላይ ጥርጣሬ ለማስፋፋት የምናቀርበውም ሐ
ሳብ ተቀባይ እንዳያገኝ ፣ ከተራማጅ ኢትዮጵያውያን ጋር እን
ዳንተባበር ለማድረግ ነው::" ይላሉ(ገጽ 38 ሥርዝ የተጨመረ)
እኔ ግን እዚህ በወሬ ላይ በልመሠረት የጽሁፋቸው ዋና ዓላማ
—ምናልበት የነበረ ጊዜ ዓላማ — የቀደሞዎቻችን የማህበር መሪ



ዎች ለማሳጣት ፣ ተማሪዎችንና ተራማጆችን እርስ በርስ ለማጋ
ጨትና የራሳቸውን "ንጹሕ ረቮሉሽናዊነት" ለማሳየት ነው እላለ
ሁ:: ከጽሁፋችን ይህንን ለመተርጐም አትችልም ፣ አይፈቀድል
ህም ይሉኝ ይሆናል? ወይንስ በጽሁፋቸው ገጽ 36 ላይ እንደ
ሚሉት ፣ "... ተማሪዎች የሚወስዱት ፖለቲካ አቋም የተጨበ
ጨ አቢይ የፖለቲካ ውጤት ስለማያስከትል በቃልና በጽሁፍ የሚ
ገለጽ "አቋም" ሁሉ መመሰሸር እንደሌለው አቋም (ኮሚትመንት)
ሊወሰድ አይቻልም" እና በጽሁፋቸው የተገለጸው ሁሉ(ኮሚትመ
ንት" አይደለም ብለው ይታለፍ ? (በነገራችን ላይ፣ "...ተማሪ
ዎች የሚወስዱት የፖለቲካ "አቋም" የተጨበጨ አቢይ የፖለቲካ
ውጤት ስለማያስከትል..." የሚለውን ፣ በገጽ 32 ላይ ፣
" ማንኛውም ይኸንን እንቅስቃሴ (የበኼሮች እንቅስቃሴ) የሚደ
ገፍ ተግባር (የተማሪዎች አንዱ ውሳኔ እንኳን ቢሆን) በሕዝቡ ከ
ተሰማ ፣ አዲስ ዓይነት ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ይቋቋም በሚል
አርእስት ከተጻፈ ሺህ የ"ታጠቅ" ጽሁፍ የበለጠ የፖለቲካ ውጤ
ት ያስከትላል::"(የመጨረሻው ሥርዝ የተጨመረ) ከሚለው ጋር አ
ንባቢ ያስተያይ! "ያስከትላል" ወይስ "አያስከትልም"፣ ጓዶች?
መምረጥ ይሻላል::

ይህ ያልጀሪያ ጓዶች ጽሁፍ በጉባዔው ላይ ሳይነበብ
በመቅረቱ ያሳዝናል:: በመጥፎነት ከርሱ ትምህርት ሊወሰድ ይ
ቻል ነበር:: አሁንም ቢሆን ፣ የመጽሔት ቦርዱ ቢያንስ የጽ
ሁፉን ሁለተኛ ክፍል ፣ እዚህ ላይ የምንመለከተውን ፣ እንዓለ

ቢያወጣው ጥሩ ነው ባይ ነኝ፡፡ በበኩሌ የዚህን ጽሑፍ ተንኮልና ተንኮልን ለመሥራት ቢቻኮሉ ጓዶች የሚያመጡትን ውጥንቅጥ ትንተና ለማሳየት እሞክራለሁ፡፡ ስለዚህም ከሚያቀርቧቸው ነጥቦች ዋና ዋናዎችን ብቻ ከዚህ በታች አመለክታለሁ፡፡

## 1. የብሔሮች ጥያቄና የተማሪ ማህበራት መከፋፈል፡፡

ያልጄሪያ ጓዶች ስለብሔራዊ ጥያቄ ዋናነት ብዙ ጊዜ ደጋግመው ይናገራሉ፡፡ ከዚህ በላይ እንደተጠቀሰው፣ በመጀመሪያው ክፍል ውስጥ ስለባላባታዊው ሥርዓት አስተዳደግና ልዩ ጠባዮች፣ ስለጊዜያዊው ጠባዩ፣ ስለኢምፔሪያሊዝም፣ በኢትዮጵያ ስላሉት ሕብረተሰባዊ መደቦች፣ ስለመሠረታዊ ቅራኔዎች፣ ስለድርጅት ጥያቄና ስለዚህ ስለብሔራዊ ጉዳይ ጽፈዋል፡፡ ለነዚህ ሁሉ — ቢያንስ ሰባት — ስሩሬ አርእስቶች ከዋሉት 26 ገጾች የመጨረሻው አርእስት — ብሔራዊ ጥያቄ — ለብቻው አምስት ገጾች ይዘአል፡፡ እንደዚሁም ከሁለተኛው ክፍል ፷8 ገጾች በቀጥታም ሆነ በዘወርዋራ መልክ ለዚህ ለብሔሮች ጥያቄ ከሁሉ የበለጠ ቦታ ተሰጥቶታል፡፡

'' ጉዳዩ በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያን የፖለቲካ ሥርዓትና ኢኮኖሚ ከናጉት ጉዳዮች ዋናው ይኸው



የብሔሮች ጉዳይ ስለሆነ ነው፡፡ የገዥው መደብ በስንት ሺህ የሚቆጠር ሠራዊት ያሠለፈው፣ በጀቱ በዓመት ዓመት የሚናጋበት፣ ፈላጭቆራጩ ነጋሢ ከአገር አገር ነጋ ጠባ የሚንጠለጠለው፣ ጠላቶቹ ከሚሉቸው ጐረቤት አገሮች መሪዎች ጋር ለመስማማት ግዛትን ቆርጦ የሚሰጠው፣ መላ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲውን የመሠረተው የተጨቆኑ ብሔሮች ትግል ለመደምሰስ በሚያደርገው ጥረት እንጂ በሌላ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ወይም በሌላ የፖለቲካ ፕሮብሌም ምክንያት አይደለም፡፡ በኢትዮጵያ አሁን ያለው ከፍተኛው የፖለቲካ ፕሮብሌም የተጨቆኑ ብሔሮች ትግል ነው፡፡'' (ገጽ 32 ስርዝ የተጨመረ)

'' የጉዳዩን እውነት ዝቅ ለማድረግ...'' ሊሉች ሞክረዋል፡፡ (ገጽ 33) ግን ይህ ብቻ አይደለም፡፡

'' በኢትዮጵያ የብሔሮች ጉዳይ በቻይና ከነበረው አሁንም በቪየትናም ወይም በላኦስ ካለው (ማለት በኢምፔሪያሊዝም በሚጨቆኑ አገሮች) የበለጠ ዐቢይ ጉዳይ ነው፡፡ ስለዚህም በኢትዮጵያ አዲስ ዓይነት ዲሞክራሲያዊ ረቮሉሽን ይህ ጉዳይ በነዚህ አገሮች ረቮሉሽናዊ ፕሮግራም ከተሰጠው ይበልጥ ከፍ ያለ ቦታ ሊሰጠው ይገባል፡፡ ይህም ረቮሉሽኑ የብሔሮችን መብት ሙሉ በሙሉ (የመገንጠልንም መብት ጨምሮ) በግልጽ

ደገኛ መሠረት አለበት:: "(ገጽ 8 (ሰርዝ የተጨመረ))

እኔ እስከማውቀው ድረስ፣ የቻይና፣ የቪየትናም፣ የላኦስ ሬፐብሊካዊ ፕሮግራሞች የብሔሮችን መብት "ሙሉ በሙሉ" በይደገፉ አልወጡም:: ከነዚህ ፕሮግራሞች አንዳንዶቹን መጥቀስ ያስፈልጋል::

የቻይና ኮሙኒስት ፓርቲ በ1945 ዓም ፕሮግራሙ ስለብሔሮች (ማይኖሪቲ ናሽናሊቲስ) እንዲህ ይላል:—

"In 1924 Dr. Sun Yat-Sen wrote in the Manifesto of the First National Congress of the Kuomintang that "The Kuomintang's Principle of Nationalism has twofold meaning, first, the liberation of the Chinese nation, and second, the equality of all the nationalities in China" and that "the Kuomintang solemnly declares that it recognizes the right to self-determination of all the nationalities in China and that a free and united republic of China (a free nation of all the nationalities) will be established when the anti-imperialist and anti-warlord revolution is victorious".

The Communist Party of China is in full agreement with Dr. Sun's policy on nationalities as stated here." Mao Tsetung - Selected works Vol. III pp. 305-306.

የኢንዶቺና ኮሙኒስት ፓርቲ — ያሁኑ የሠራተኞች ፓርቲ— በ1935 የመጀመሪያ ጠቅላላ ስብሰባው ላይ ያሳለፈው ውሳኔ እንደሚከተለው ነው:— (ከፈረንሣይኛ የተተረጎመ)

"ዝብዬ፣ በ1932 በፓርቲው የወጣ ፕሮግራም



እንደተጠቀሰውና ኮሙኒስት ኢንተርናሽናል በተስማማበት መሠረት፣ ብሔሮች የወደፊት ዕድላቸውን ለመወሰን መብት እንዳላቸው ያውቃል:: የራስን ዕድል መወሰንና ኢምፔሪያሊስቶችን ለመዋጋት በጥብቅ እንዲመሆን የሚባሉት መመሪያዎች በጣም ቀና መሆናቸውን ለብሔሮች መገለጽ የግድ አስፈላጊ እንደሆነ ፓርቲው ለቅርንጫፎች ሁሉ ያስታውቃል:: ኮሙኒስት ፓርቲው ብሔሮች ሁሉ ለሙሉ ነፃነት መብት እንዳላቸው ያውቅላቸዋል:: አንዱ ብሔር በሌላው በተጭቶም ሆነ በጀ አዙር የሚያደርገውን የቅኝ አገዛዝ ሥርዓት፣ ማንኛውንም ዓይነት ጭቆና በጥብቅ ፓርቲው ይቃወማል::" Etudes Vietnamiennes No.15 p.12

እንደዚሁም የደቡብ ቬየትናም ብሔራዊ የነፃነት ግንባር ፕሮግራም:—(ከፈረንሣይ የተተረጎመ)

1. ብሔሮች ለአውቶኖሚ ያላቸውን መብት በተጠበቀ ከሥራ ላይ ማዋል
   - በትልቁ የቬየትናም ቤተሰብ ውስጥ ብሔሮች በሉበገው ክልል አገሮች አውቶኖሚ ያላቸው ክልሎች (ዞኖች መፍጠር
   - ለብሔሮች እኩልነት ትኩረት ማድረግ:: ብሔሮች ሁሉ በቋንቋቸውና በጽሁፋቸው ለመጠቀምና ለማዳበር ነፃ ናቸው:: ጊዜያቸውን የብሔር ልዩ

ነትና በነፃ ማስገባት (አሲሚሌት ማድረግ) የሆነውን የደየምን ፖሊሲ ማስወገድ

– ብሄሮች በሕዝቡ ወቀሳሳ ደረጃ እንዲደርሱ ኢኮ ኖሚያቸውንና ዕውቀታቸውን በሉበት በማዳበር ሥጦታ ያላቸውን የነዚህን ብሄሮች ልጆች በማሠልጠን መር ዳት።

እነዚህ የተጠቀሱት ስድስት ፕሮግራሞች የሬፐብሊሽናውያን ፕሮ ግራሞች ናቸው። ያልቿሪያ ጓዶች በነዚህ "ሬፐብሊሽና ፕ ሮግራሞች በተለመው ይዘልቃ ዘና ያለ ቦታ የሚሉት" "የመ ንግሥታንም መብት ጠቀም" የሚለው ተጨማሪ በለመታየቱ ይመ ስለኛል። ይሁንናም በጽሁፍ ብቻ ብይሆን በተግባር፣ የደ ርግ ቪየትናም አርበኞች እደሚሉት በዝርዝሩ፣ በእውነት፣ እነዚህ ፕሮግራሞች የብሄሮችን መብት በሥራ ላይ እንዳዋ ሉት ዓለም በሙሉ ያውቃል። ነገ ጓዶች "ቦታ" ቢሉ በፕ ሮግራሙ ውስጥ የሚሰጠው ተራ ማለታቸው ከሆነ፣ በኢትዮጵያም ቢሆን የመጀመሪያው ነጥብ "የብሄሮች ጥያቄ" መሆን አይገ ባውም። ጓዶች ቢያነቡ ዘጻጻሩቸው ሊገለብጡት የሞከሩት የራሲያ ሬፐብሊኪን ፕሮግራም እንኳን የብሄሮችን ጥያቄ የመ ጀመሪያው ነጥብ አላደረገውም (ራሲያ አሥር እጅ የበለጠ ሕ ዝብ ከኢትዮጵያ ፊውዳላዊ ሥርዓት ነጠቀን ነበር!) በቻይና ው ፕሮግራም ዘጠነኛ፣ በደብሊ ቪየትናም ስድስተኛ ነጥብ ነው። ይህም ትክክለኛ ነገር ነው። "ጥና ጉዳይ"፣ "ከናተኛ ፕሮብሌም"፣ "አውራ ጉዳይ"፣ "ዐቢይ ጉዳይ"



ቢሉ በግልጽም በይናገሩት ያልቿሪያ ጓዶች የሚፈልጉት ለብ ሄሮች ጥያቄ የመጀመሪያውን ቦታ ለመስጠት ይመስላል። ነገ ን እንደተበለው ግልጥ አድርገው አልተናገሩትም፣ በሌላ ቦታ ደግሞ:—

"በአሁኑ የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ሌሎች የሁለተኛ ደረጃ ቅራኔዎች አሉ። እነዚህም ቅራኔዎች በወ ሳት ጣገን፣ በጥገኛ ቡርዥዚውና በፊውዳሉ መደብ መካከል፣ በሠራት በኩል፣ የፊውዳሉ መደብና የጥ ገኛ ቡርዧው መደብ በአንድ በኩል ሆነው ከኢም ፔ ሪያሊዝም ጋር ያላቸው ቅራኔ፣ በሕዝቡም ወገን፣ በብሄራዊ ቡርዧው መደብና በላዘአደሩ መደብ መካ ከል፣ በጠቋን ብሄሮችና በተጠቋን ብሄሮች መካከል ያለው ቅራኔ በአሁኑ የኢትዮጵያ ሁኔታ ብርቱ ቅራ ኔ ቢሆንም የመደብ ቅራኔ ስላልሆነ በትክክለኛ የ ሬፐብሊካና ፖሊሲ አማካይነት ሊፈታና ለሬፐብሊኩኑ እድገት መሰናክል እንዳይሆን ለማድረግ ይቻላል"

(፳፪) ይላሉ።

እነዚህም ላይ ብዙ የተምታታ ነገር አለ። ይሁን እንጂ፣ እዚህ ላይ በጠቋንና በተጠቋን ብሄሮች መካከል ያለው ቅ ራኔ ከሁለተኛ ደረጃ ቅራኔዎች የመጨረሻው ሆኖ መቀረቡን በደንብ እናስተውል። ለብሄሮች ጥያቄ "ዐቢይነት፣ ከፍተ ኛነት ሀዘተ" በጽሁፋቸው ውስጥ የተሰጠውን ቦታ እዚህ

ሳይ ስለመደብ ቅራኔ ዋናነትና ስለብሔራዊ ጉዳይ «የሁለተኛ ደረጃነት» ከተጠቀሰው ጋር ያመሳሰለ ማንም ሰው ሁለት ነገሮችን ሊረዳ ይችላል:: (ሀ) ይህኛው ያሁኑ ጥቅስ የቀሩትን ሁሉ ስለ'ቀናነት' የሚያወሩትን ቢቃረንም አንዚያኞቹ በብዛትም በጥብቅነትም (በኤምፋሲስ) ስለሚበልጡት ይህኛው የተምታታው ጥቀስ ለፍርሙ ያህል፣ ከንገት በላይ፣ ለንገሩ ብቻ የተባለ ነው:: (ለ) ስለብሔሮች በተጠቀሰ ቦታ ሁሉ ጓዶች የፕሮብሌሙን አንዱ ወገን ብቻ — የመገንጠልን መብት — አጋንነው፣ ሌላውን እኩል መነገር ያለበትን — የብሔሮችን በሳብአደር ኢንተርናሽናሊዝም መተሳሰር ጉዳይ — አድበስበሰውት አልፈዋል:: እዚህ ላይ ከሁሉ የተቆጠበ ለመናገር የምችለው ነገር ጓዶች አደገኛ መንገዱ መያዛቸውንና በጠቀሳሳያም በጽሑፋቸው ትልቅ ያስተባበብ ውዝግብ መፍጠራቸውን ነው::

በዚህኛው ነጥብ ላይ እመለሰበታለሁ:: ግን ከዚህ በላይ ከተሰጡት ጥቅሶች ውስጥ አንዱ የሚያስደንቀው የሀይለ ሥላሴ መንግሥት «መላ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲውን የመሠረተው የተጨቆኑ ብሔሮችን ትግል ለመደምሰስ በሚያደርገው ጥረት እንጂ በሌላ ... አይደለም» የሚለው ነው:: በኔ አስተያየት፣ ይህ ፈጽሞ ከእውነቱ የራቀ፣ ከላይ የተጠቀሰውን የብሔራዊ ጥያቄን «ዐቢይነት» እንደገና ለማጉላትና ለማጋነን ብቻ ተጠባውን እውነት የሚያጣምም ክርክር ነው::



ጓዶች ይህንን ሲሉ በምን ላይ ተመሥርተው ነው? ምናልባት ከዚህ በላይ እንደጠቀሱት የሀይለ ሥላሴ መንግሥት ከአረብ አገሮች — በተለይም ከሱዳን ጋር — በቅርቡ መቨረኩን፣ ምናልባትም ሀይለ ሥላሴ ቻይናን መጎብኘቱንና ከዚያች ረቮሉሽናዊ አገር ጋር ዲፕሎማቲክ ግንኙነት መፍጠሩን በመመልከት ነው:: ከነዚህ ሁለት ሁኔታዎች የሀይለ ሥላሴ መንግሥት በተለይ የኤርትራን ትግል ለብቻ ለማውጣትና (አይሶሌት ለማድረግ) ለመደምሰስ እንደፈለገ በርግጥ ለመገመት ይቻላል:: ግን ይህ የፖሊሲው አንዱ ወገን ብቻ ነው:: ለዚያውም ከቻይና ጋር የተፈጠረውን ግንኙነት በሁኑ ጊዜ — ቻይና ከዓለም አገሮች ሁሉ ጋር በመንግሥት ደረጃ ግንኙነትን ለመፍጠር በተነሳችበት በሁኑ ወቅት — በዚህ ብቻ ለመተርጎም ፈጽሞ አይቻልም::

ማንም እንደሚያውቀው፣ የሀይለ ሥላሴ መንግሥት የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ከሀያ ዓመታት በፊት ጀምሮ የተመሠረተውና አሁንም የሚቆመው ከአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ጋር በተቀቀለው ፀረረቮሉሽናዊ ውል ላይ ነው:: ከዚያ ወዲህ ያሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ቀኝ እጅ የሆነው ጽዮኒዝም በዚህ ወዳጅነት ተጨምሮበታል:: ይህ ፀረረቮሉሽናዊ ወዳጅነት ከመጀመሪያውም የብሔሮችን ትግል ለመደምሰስ የታቀደ ባይሆን በጠቀላላው በንጉሡ ነገሥቱ መንግሥት አንዳችም ዲሞክራሲያዊ ለውጥ እንዳይደረግ፣ በተለይም ከጦርነቱ በኋላ በቅርብ ምሥራቅና በመላ አፍሪካ ከነፈሰው የለውጥ ነፋስ ኢትዮጵያን ለመከለል

የተደጋገመ ነው፡፡ ለመድገም ያህል ግን አንዳችም ለውጥ እንዳይደረግ፣ ማለት ሌላው ቀርቶ በባባቢው እንደተደረገው አንዷን የከበርቴውና የንኡስ ከበርቴው መደቦች ሥልጣኑን እንዳይወስዱ ለማድረግ፣ የበላባቶ መደብና የቢሮክራሲ ከበርቴው ሥልጣንና ጥቅም ፈጽሞ እንዳይነካ ነበር፣ ነው፡፡ የሀይለ ሥላሴ መንግሥት «ያፍሪካ አንድነት»፣«የገለልተኛ» የ«ሴኩሬቲ ኮሌክቲቭ»፣ የ«ሰላም»ና የ«ዕርቅ» ፖሊሲውን ሁሉ የሚጉነጉነው በዚህ ምሰሶ — ማለት ካሜሪካን ኢምፔሪያሊዝምና ከጽዮኒዝም ጋር ባለው ፀረረቮሉሽናዊ ወዳጅነት — ዙሪያ ነው፡፡ እርግጥ ረቮሉሽን በቀጥታ የብሔሮችን ነፃነት ይመለከታል፤ ግን የብሔሮች ነፃነት ወይም ትግል የረቮሉሽን ዋና እንቀስቃሽ አይደለም፡፡

የሀይለ ሥላሴ መንግሥት በዚህ ፖሊሲ አማካይነት ከራስጠጉሩ እስከግርጥፍሩ የታጠቀ ሠራዊት ገነባ፡፡ ይህንን ሠራዊት አሁንም እንዳጠነከረው ነው፡፡ ግን ይህ ሠራዊት የገዢው መደቦች መሣሪያ እንጂ የአማራ ብሄር መሣሪያ አይደለም፡፡ ያለበለዚያ ጉዳም በ1968 እንደዚያ ባልተጠፋጠፈ ነበር፡፡«መላው» የሀይለ ሥላሴ መንግሥት የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ የተመሠረተው የብሔሮችን ትግል ለመደምሰስ በሚያደርገው ጥረት ላይ ነው ከተባለ በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ህብረተሰብ ውስጥ ያለው ዋና ቅራኔ የብሔሮች እንጂ የመደብ አይደለም ማለት ነው፡፡ በጭራ፣ የዘመኑ«መላ» የመንግሥቱ ፖለቲካ እንደምኒልክ ዘመን ብሔሮችን ለማስገበርና ለመያዝ፣ በዘመቻ ላይ የተመሠረተ ነው



ማለት ነው! ያልጄሪያ ጓዶች ለብሔሮች ጥያቄ የሚሰጡትን «ርቢይነት» አጋንነው ከቅዠት ላይ በማድረሳቸውም በላይ፣ እነርሱ ራሳቸው የሚያቀርቡትን ጊዜአዊ መሪአጋብ — «የፈላጭ ቆራጭ ነጋሢ አገዛዝ ይደምሰስ»፣«ዴሞክራሲያዊ ረፓብሊክ» (ገጽ 6)— በዚሁ ያፈርሱታል፡፡

ዋናው የሀይለ ሥላሴ መንግሥት ፍርሃት የገዢው መደቦች በማንኛውም አቢዮን እንዳይገለበጡ ነው፡፡ በ1969 ያሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ወኪል ሮጀርስ አዲስ አበባ የሄደ ጊዜ፣ ብዙ የዓለም ጋዜጦች በግልጽ እንደጻፉት ሁሉ፣ ሀይለ ሥላሴና አኪሊሉ እንደገና የመሣሪያ እርዳታ ሲጠይቁት «ኮሙኒዝም ወደምሥራቅ አፍሪካ ገብቷል» በሚል ማመካኛ ነበር፡፡ የሀይለ ሥላሴ መንግሥት ዋና ፍርሃት ረቮሉሽን መሆኑን ያበያል፡፡ ይሁን እንጂ በኢትዮጵያ የሚደረገው ረቮሉሽን ለተጠቁ ብሄሮች ነፃነትን ማምጣቱ ስለማይቀር፣ ወይንም ዛሬ የብሔሮች ትግል ተጋግሎ ስለሚታይ፣ ይህንን ጥያቄ እንደዋናው የጊዜው ቅራኔ አድርጎ መጥጋቱና የመጀመሪያ ቦታ እንዲሰጠው መጠየቅ የመደብን ትንተና ወደጎን መጣል ነው፡፡ በመጠረሻም፣ የብሄሮች ትግል እራሱ ዙሮ ዙሮ የመደብ ትግል መሆኑን መርሣትም ነው፡፡ ያልጄሪያ ጓዶች አዝማሚያ እጅግ በጣም ያሳስባል፡፡

ያልጄሪያ ጓዶች ስለብሄሮች ጥያቄ "ዋናነት" በጠቅላላው ምን እንደሚሉ አይተናል፡፡ በነገምት፣ ይህንን

በደበባይና በገለጸ «የብሔሮች ጥያቄ የኢትዮጵያ ረቮሉሽን ፕሮግራም የመጀመሪያው ነጥብ መሆን አለበት» ማለቱ ብቻ የቀረበትን አቋም ያስወሰዳቸው በኤርትራ ግንባር ሥር ጥገኞችን የመፈለግ ያድርባይ (ኦፖርቹኒስት) ፖለቲካቸው ሰይሆን አይቀርም:: ይህም ወደፊት የበለጠ በግልጽ ሰይታይ አይቀርም:: ይሁንናም በሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ረቮሉሽን ፕሮግራም ይበልጥ የሚመለከተን፤ ያልጂሪያ ጓደኞች፤ የተማሪ ማህበራትን የከፋፈለው ብሔራዊ ጥያቄ ነው ማለታቸው ነው:: በዚሁ ጥያቄ ላይ በተደረገው ክርክር ምክንያት የኢትዮጵያ ተማሪዎች «በብሶት ቁና ቁና ክፍሎች ተከፍለዋል» ይሉና፤ የመጀመሪያው ክፍል የሳብአዴሩ ወገን — እነርሱ —፤ ሁለተኛው ክፍል የነዑስ ከበርቴ ሹምከሬቶች «በሸቪኒስቶች አንገት ላይ የተጋደመውን ሰይፍ ለማደልደም» የሚጥሩ (33) — በዉሮፖው ማህበር ውስጥ ያለው —፤ ሰስተኛው ክፍል የትንሽ ረብ፬ ሬቪስቶችና የፊውዳሉ መደብ አንድነት — የመጀመሪያው በሚሪካው ማህበር አመራር ውስጥ የነበሩትን ያመለክታል — መሆናቸውን በሰፊዉና በተራቀቀ " ትንተና " ሊያሳምኑን ይሞክራሉ:: ይህንን አሚስ የኢትዮጵያ ተማሪዎች የመደብ አከፋፈል ጥያቄን ትቼ፤ «የብሔሮች ጥያቄ የአሜሪካውን ማህበር ከፋፈለ ወይ?» የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ እሞክራለሁ::

ለዚህ ጥያቄ ከመመለሴ በፊት ያልጂሪያ ጓደኞች አረባቸው በጠቀሳሳው ስለ ተማሪ ማህበራት የመከፋፈል ችሎታ የሚናገሩትን መጥቀስ የሚጠቅም ይመስለኛል::



በጽሁፋቸው ሁለተኛ ክፍል ፤ በመጀመሪያው ገጽ ላይ ገጽ 27 እንዲህ የሚል አለ ፤

«የተለያዩ መደቦች የፖለቲካ ፓርቲዎች በሉበት አገር በፖለቲካ የነቁ ተማሪዎች የተለያዩት ፓርቲዎች አባሎች ወይም ደጋፊዎች ይሆናሉ ፡ በዚህም ምክንያት በፓርቲዎች መሀከል "የሕብረት ግንባር" በሌለበት ጊዜ በተለይም በፓርቲዎች መከል ትልቅ ቅራኔ በሚኖርበት ጊዜ ተማሪዎች የተለያዩ የተማሪ ማህበሮች ሊያቋቁሙ ይችላሉ:: (ተማሪዎች በህብረሰቡ የመደብ ትግል ውጭ አይደሉም!) በአገራችን በአሁኑ ጊዜ ተማሪዎችን ሊበፉፍሉ የሚችሉና ተማሪዎች የሚደገፏቸው የታወቁ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሉም :: ስለዚህ ተማሪዎች የሚለያዩበትና ተቃዋሚ ድርጅቶች የሚፈጥሩበት በቂ ምክንያት የለም::»

በጣም ቀላል አባባል ነው :: እኔም እንደዚሁ "በቂ ምክንያት የለም" እላለሁ :: ሆኖም በሚረካው ማህበር" ድርጅታዊ መከፋፈል" (ገጽ 32) ደርሷል :: ታዲያስ ፤ የብሔሮች ጥያቄም ፡ በዚህ በላይ ጓዶች በሚሉት መሠረት ከሆነ «በቂ ምክንያት» አልነበረም ማለት አይደለምን ? ወይንስ «ብሔርና" ፓርቲ» አንድ ናቸው ሊባል ነው ?

እኔ እንደማውቀው ፤ ከተከፋፈሉት በዎች እንደሰማሁት ዜና ከሆነ ፤ ያሜሪካውን ማህበር የከፋፈለው እውነተኛ

ምክንያት የብሄሮች ጥያቄ አልነበረም :: እርግጥ ይህ ጥያቄ በማህበሩ ውስጥ ብዙ ክርክርንና ግጭትን አስከትሉ አል :: እውነተኛው መከፋፈል የመጣው ግን የብሄሮች ጥያቄ ከመነሣቱ በፊት ነበር :: ይህንን ለመረዳት ፣ ያልጀሪያ ጓደኞች "ለተወበነ አሳማ" የሚሰጡትን ፍርድ እንዳለ በመቀበል ፈንታ የተጠበጠ በሐቅ ላይ የተመሠረተ ምርመራ ማድረግ ያስፈልጋል :: ማህበሩ የተከፋፈለው እንዴት ነው?

በታህሣሥ 1969 ያዲስ አበባ ተማሪዎች እልቂት በኋላ ፣ ቀደም በአዲስ አበባው ማህበር ውስጥ የነበሩ መሪዎች ወደውጭ አገር በተለይም ወደ አሜሪካ ወጡ :: እነደአልጀሪያ ጓደኞች ሁሉ ፣ እነዚህም ጓዶች በገቡበት ሲገቡ በውጭ አገር ያሉት ማህበሮች ለመሣሪያ ትግል የተዘጋጁ ድርጅቶች፣ተሉ እነርሱን ተቀብለው አሠልጥነው ዘመን ኛ አስይዘው ወደጦሩ ሜዳ የሚልኩአቸው መስሏቸው ነበር! ነገር ግን እነዚህ ማህበሮች <u>የተማሪ ማህበሮች ብቻ</u> መሆናቸውን ሲያዩ ያደረባቸውን ብስጭት ፣ በብስጭትም አልፎ "የቀደሞዎቹን" (ቢትሬንስ የተባሉትን) ወደ መቃወም ማለፋቸውን በቀላሉ ለመረዳት ይቻላል :: ይህንን በሚገባ ለመረዳት እንዱ ጊዜ በሰኔ 1971 የሚጽፈውን ማየት ይበቃል:: ይህ ጽሑፍ ምንም እንኳን የብሄሮች ጥያቄ በመነሣቱ ከሦስት ወሮች <u>በኋላ</u>-ግን ከ19ኛው ያሜሪካው ማህበር ጠቅላላ ጉባኤ ሁለት ወሮች <u>ቀደም</u>-<u>የታተመ</u> ቢሆንም ፣ የመሩ



ፊሉን እውነተኛ መሠረት በደንብ የሚገልጽ ስለሚመስለኝ በሰፊው እጠቅሰዋለሁ :: —

"... if we have to point out a particular section of the Ethiopian Student movement for <u>the most serious failures</u>, then we would point out the student organisations aboard.
First of all both (i.e. at home and aboard) have, sofar, failed to train and produce ideologically-mature politically and organisationally trained revolutionary intellectuels who could initiate the <u>founding</u> of a revolutionary political organisation. Ethiopian students abroad under_take higher university studies, live in political systems that provide all the conditions and facilities for acquiring revolutionary theories and for easily learning the theories and practice of political (legal or illegal) organisations; therefore, it is only understandable and justifiable that Ethiopian revolutionary students <u>inside</u> the country <u>have patiently waited for their "elders" to take the initiative in founding the necessary political organisation. However, ESUNA and ESUE have so far, disappointed the revolutionary students inside..."</u>

" we believe that the immediate tasks of the Ethiopian Student Movement, all Ethiopian revolutionary intellectuals are to : " Organise a Proletarian Party ", "Organise the Working class" " (p. 58)

" We are conviced that the over-due "urgency" of a Proletarian Party should be reason enough to compel "revolutionary" students to voluntarily interrupt their academic careers, their under-graduate or post-graduate studies and physically integrate with the working class..." (p. 62)



በ1969–70 ከገር ቤት ለወጡት ጓዶች የውጭ ማህበሮቻችን የፖለቲካ ድርጅቶች ሆኖ አለመገኘት በጣም "አበሻዊ" ነገር ነበር ። በዚህ በላይ የተጠቀሰው ጽሑፍ በደንብ እንደሚያስየው ፣ ረቮሊሺኑ ፣ በተለይም የመሣሪያ ትግሉ ፣ "በቅርቡ" በኢትዮጵያ የሚደረግ ይመስላቸው ነበር ። ስለዚህም የተማሪ ማህበራት በንዑ ባልታወቀ መንገድ ወደፓርቲ ተለወጡ(በዚህ በላይ ሁለተኛውን ጥቅስ በደንብ ማስተዋል ያስፈልጋል) ቶሉ የሠራተኛውን መደብ ማደራጀት ይኖባቸዋል! የረቮሊሺኑ "አጣዳፊነት" የዩኒቨርሲቲን ትምህርት አንቆን አስከመጠረስ የሚያቆይ አይደለም!! ይህ ብቻ አይደለም ። በ1971 በአሜሪካ በቀጥታ ወደጫካ ለመግባት የተዘጋጁ ጓዶች ነበሩ ። ከነዚህ ውስጥ ብዙዎች በኋላ የቀደሞውን የማህበር አመራር "ፀረረቮሉሺዊነት ለማስየት የሚችሉ ነበሩ" ።(በነገራችን ላይ ከዚህ በታች እንደምንጠቀበው ሁሉ ፣ ያልጀሪያ ጓዶች ሠናይ ልኪ የመደራጀት "ምስጢር" ስለወጣባቸው በጣም በንዴት ይናገሩ ። "ምስጢሩ" የወጣው ESUNA - Bimonthly በተባለው ጽሑፍ በነሐሴ 1971 ነው ። በዚህ በላይ የተጠቀሰው ጽሑፍ የወጣው በሰኔ 1971 ቢሆን ፣ ስለ "ሳብ አደር ፓርቲ" ማደራጀት አስቸጋይነት ተማሪዎች በየቤታቸው ባሉት የፓርቲውን ቅርንጫፎች(ሴሎች)እንዲያቋቁሙ... ወዘተ እንደዚህ በአደባባይ በቀስቷሽነት(ፕሮፖጊሽን) ሲለፍፍ በሠናይ ልኪ "ምሥጢር" ማውጣት ምንም ያህል አይለይም ። ያልጀሪያ ጓ

ዶች በሁኑ ጽሑፋቸው ይህንን ከዚህ በላይ የተጠቀሱትንም
ጽሑፍ ባይወቁቡ ማለፋቸው ያስገርማል!)

በ1970 መጨረሻ ገደማ፣ በኒውዮርክ ቻፕተር
ውስጥ በቀድሞዎቹ መሪ ጓዶችና በዲሲቶች ጓዶች መካከል
ንትርክ ተፈጠረ:: ነገሩ የተጀመረው የሞተው ጓድ መስፍን
ሃብቱ በቀድሞዎቹ የታወቁ መሪዎች ላይ፣ "እናንት ጸጸብት
ናችሁ፣ የወንበር ረቮሉሽናውያን ናችሁ፣ ረቮሉሽን ለማድ
ረግ አትፈልጉም፣ የምትፈልጉት ቁጭ ብላችሁ ቲዎሪ ማውራት
ብቻ ነው ...ወዘተ" የሚል ክስ ጭኖ የማህበሩ አሠራር
ዘዴ እንዲለወጥ በጠየቀበት ጊዜ ነው:: በመጀመሪያ ላይ
እነዚህ አዲስ ጓዶች የቀድሞዎቹን ቢከስሱ ስለተማሪ ማህ
በር አሠራርና ዓላማ የተዘበራረቀ አስተያየት የነበራቸው
ይመስላል:: እንዴ ለምን እዚህ ቁጭ ብለን እንለፈልፋ
ለን፣ የደፈጣ ውጊያ እንጀምር እንጂ ይሉ ነበር:: በ
ሌላ ጊዜ ደግሞ የተማሪው ማህበር ማርክሲስት—ሌኒኒስት
መሆን አለበት ይሉ ነበር ይባላል:: ...በጠቀሳሰው፣
ከተፈጠረው ውዝግብ የተነሣ በሁለቱም ወገኖች በኩል ብዙ
ስሕተቶችና አለመግባባቶች ባይደረጉ አልቀሩም:: ከጥቅምት—
ህዳር 1970 ጀምሮ የቀድሞዎቹ መሪዎች በሞሳጉደል ከቻ
ፕተሩ አመራር ተወገዱ:: በተጨማሪም፣ ይህ በኒውዮርክ
ቻፕተር ውስጥ የተፈጠረው መቃቃር ወደሌሎችም ቻፕተሮች
በተለይም ወደምዕራብ — ተሠራጨ:: ባጭሩ፣ አርገጠኛው



የማህበሩ መከፋፈል የወጣው በዚህ በ1970 መጨረሻ
ላይ ነው::በኒውዮርክ ቻፕተር ውስጥ በዚህ ውዝግብ
የተከፈሉት ጓዶች ምናልባት አንድ ቀን ሙሉ ታሪኩን
በሐቅ ካወጡትና በሁለቱም በኩል ረቮሉሽናዊ ሂስና
የግል ሂስ ከተደረገ ይህንን እውነት በግልጽ ለማየት
እንደሚቻል ፈጽሞ አልጠራጠርም::

የማህበሩ እውነተኛ መከፋፈል በዚህ አኳኋን
ሲሆን፣ በማርች 1971 የጥላሁን ታከለ ጽሑፍ በኒው
ዮርክ ኒውስሌተር ሲወጣ፣ ቀድሞ በማህበሩ ውስጥ ያዲስ
ችና የቀድሞዎች ወገን ሠርተው ተሠልፈው ነበር:: ገና
የብሔራዊ ጥያቄ ጉዳይ ከመነሣቱ በፊት እንደ "ፀረረቮሉ
ሽናውያን" ወይንም እንደ "የውሸት ረቮሉሽናውያን" የተሰየሙት
የቀድሞው አመራር ጓዶች፣ በጥላሁን ታከለ ጽሑፍ አማካይ
ነት ያዲሱ ግራክንፍ ምሣር መውደቂያ ሆኑ:: የጥላሁን
ታከለ ጽሑፍ "ጠላትነታቸውን" አረጋገጠ:: ማለት፣ የብሔ
ራዊ ጥያቄ ነገር ቀድሞ የደረሰውን መከፋፈል አጸደቀው::

ያሜሪካው ማህበር በ17ኛው ጉባዔ ላይ ስለ ሪጂ
ናሊዝም ያወጣቸውን ጽሑፎችና ውሳኔዎች እኔም አልስማማባ
ቸውም:: እንደዚሁም የኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ማህ
በር በ6ኛው ጠቅላላ ጉባዔው በ1967 ያወጣቸውን ውሳኔ
ዎች — ምናልባትም ጥላሁን ታከለ እራሱ ያን ጊዜ የተስማ
ማባቸውን ውሳኔዎች — እቃወማለሁ::(ውሳኔው በዚህ ጽሑፍ
ጋር ተያይዟል::) ያልጄሪያ ጓዶችም ምናልባት ያኔ ሲፀፅ

ማሙበት አልተሩም::) የዛሬ አራት ዓመት ስለብሔራዊ ጥያቄ የነበረን አቋም ይህንን የኪዩቶማን የ1967 ውሳኔ ይመስላል:: ነገር ግን ይህንን ውሳኔ ዛሬ ስለ ምታወመው ያኔ ውሳኔውን ያሳለፉት ጓዶች «ሶሻልሾቪኒስቶች» ናቸው፣ «በአፍ ሶሻሊስቶች በሥራ ሾቪኒስቶች» ናቸው አልልም:: የጥሳሁን ታከለ ጽሑፍ ያ17ኛውን ያሜሪካን ማህበር ገብዬ ጽሑፎች ደራሲያችን «ሶሻል ሾቪኒዝም» ሲያወጣ ለብዙው «ሶሻል ሾቪኒዝም» የሚለውን ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ ለሰማው ያሜሪካው ማህበር ጓዴ ሁሉ «ጠላቶች» መሆናቸውን አመለከተ::

የጥሳሁን ታከለ ጽሑፍ ይዘት ምንድነው?

የጥሳሁን ታከለ ጽሑፍ እንኳንስ በይዘቱ ቀርቶ፣ በቋንቋውም በጣጣሉም፣ በስነዘዘሩም የሌኒን ቀጥታ ገልባጭ ነው:: ሙሉ ጽሑፉ — በኒውስሌተሩ በማርች 1971 የወጣው — 38 ገጽ ሲሆን፣ ሌኒን ብቻ 31 ጊዜ ተጠቅሷል! በድምር ማርክስ፣ ሌኒን፣ ስታሊንና ማኦትሴቱንግ ከ38 ጊዜ በላይ ተጠቅሰዋል:: በጥሩ፣ ጥሳሁን ታከለ በየገጹ ማርክሲዝም — ሌኒንዝም ስለብሔሮች የሚናገረውን መሠረታዊ አሰቦች ከማስቀመጥ ሌላ ያወጣው ነገር የለም:: ይሁንናም ያልጂሪያ ጓዶች እንደሚሉት ሁሉ :—

«አንዱ ሰው የማርክስን፣ የሌኒንን ወይም የማኦን ጽሑፎች አንብቦ ለመጠቃቀስ ስለቻለ የላብአደር ወገን ሆነ፣ ወይም የላብአደሩ ርዕዮተ ዓለም ተዋህዶታል ለማለት አይቻልም:: አንዳንዱ የሀርቫርድ፣ የኦክስፎርድ፣ ወዘተ ቡርዧ ፕሮፌሰሮች እነዚህን ታላላቅ የላብአደር መሪዎች ጋናልበትም ከአብዛኛው የሠራተኛ መደብ ፓርቲ አባሎች የበለጠ አንብበዋቸዋል፣ የበለጠ ሊጠቃቅሷቸው ይችላሉ:: ነገር ግን ይህ የመጽሐፍ ዕውቀታቸው የነዚህ የላብአደሩ መደብ ፓርቲ መሪዎች ሀሳብ ተከታዮች ሊያደርጋቸው አልቻለም::» ... ገጽ 53



ይህንኑ አባባል በቀጥታ ለጥሳሁን ታከለም ለማዋል እንችላለን:: የጥሳሁን ታከለን ገልበጣ በቡርዧ ፕሮፌሰሮችም መጠቃቀስ ይበልጥ አደገኛ ያደረገው፣ በታንና ሁኔታን፣ ጊዜን ሳይለዩ፣ ሳያስላስል፣ የሌኒንን ቋንቋና አከሄዱ እንዳለ ወስዶ የቀደምቶችን ያሜሪካ ማህበር ኃላፊዎች ጠላት አድርጎ ማቅረቡ ነው:: ስለዚህም የማህበሩ መከፋፈያ ምክንያት ሌላ ሌላ ነገር ሆኖ ሳለ፣ ብሔራዊ ጥያቄ ሳዊቦች የግራ ክንፍ የቀደምቶችን ለመቃወሚያ፣ «ለማጋለጫ» ጥሩ አጋጣሚ ሆኖ ተገኘ::

ያልጂሪያ ጓዶች ስለጥሳሁን ታከለ ጽሑፍ ሲናገሩ እንዲህ ይላሉ :—

«ጽሑፉ ሐሰት ወሬ የሌለበት ከመሆኑም በላይ የታወቁ ሰዎች በግልጽ በወጡት ጽሑፍ ላይ ብቻ የተገለጸውን ሐሳብ ስህተተኛነት ከማሳየትና ደራሲያችም በነዚህ ጽሑፎች በወሰዱት አቋም ብቻ ሊሰጣቸው የሚገባውን መታወቂያ ለአንባቢያች ከመግለጽ አልፎ ተርፎ ስለሰዎች የግል

ታሪክ ወይም ጠባይ (ነገሩን ላላ ጽሑፍ እንኳን) እንደ
ቃል አይጠቀምም::! ገጽ 40 .
በእኔ አስተያየት ይህ አነጋገር ፍጹም አይገስጣ ገበዝ
ነት ነው:: የጥላሁን ታከለ ጽሑፍ በታነ፣ ጊዜንና ሁኔ
ታን በይለይ ሳኒንን በመገልበጥ፣ "ሂስ" የቀረበባቸውን ጉደ
ቾ ፈጽሞ ለመደምሰስ የታቀደ እንጂ፣ ያስተባሰበቻውን "ስህ
ተተኝነት" ለማሳየት ብቻ አልተጻፈም:: የጥላሁን ታከለ
ጽሑፍ ጉደቾ በወጡት ጽሑፍ ብቻ አይወሰንም:: በደንበ
የጉደቾን ሙሉ አቋምና "ጠባይም" ጭምር ይመለከታል:: ይህ
ንን ለማሳየት ጥላሁን ታከለ የሚጠቀምባቸውን አንዳንዱ
ሀረጎች ለጉደቾ የሚሰጣቸውን ቅጽሎች መጥቀስ ይበቃል:—

- (their) caracteristic petty bourgeois complacency. p.15
- (their) method of perfidy, distortion, ambiguity and double-talk. p.16
- they have unscrupulously distorted... p. 16
- the hypocrisy, evasion and equivocality characterising every phrase p.16
- his wish is nothing less than a slip of the tongue of a chauvinist. p.18
- royal scribe p.22
- we do not mean to humiliate our "revolutionary" friends. p.28
- the Ethiopian cadets do things in a more perfidious, more subtle, and, therefore more dangerous way, p.29
- they are past masters at the "art" of twisting and wriggling, after all p. 29



በነገራችን ላይ ያልጂሪያ ጉደቾ በጽሑፋቸው ውስጥ ደጋግ
መው "አሹሙርና ውስጠወይራ" የሬውዓል ርዕዮተዓለም መገለጫ
መሆናቸውንና ለነርሱ ትዕግስት እንደሌላቸው፣ እንደሚዘገ
ኀፏቸው ...ወዘተ ይናገራሉ:: የጥላሁን ታከለን ገልበጣ
ዓይነተኛ የሚያደርገውና ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ቅጽሎች
ብቻ እንኳን በደንብ እንደሚያሳዩት፣ ከዳር እስከዳር አሹ
ሙርና ውስጠወይራ ሞልቶበታል:: በዚህ ሁኔታ ያልጂሪያ
ጉደቾ ሲኒንንና ገልባጩን ጥላሁን ታከለን ለሬውዓል ርእዮ
ተዓለም "ተዕአናኦቻው" በመውቀስ መጀመር ይገባቻው ነበር::

እንግዲህ ስለአሚሪዞው ማህበር መከፋፈል ለመደምደም
ያህል፣ አንደኛ ነገር፣ የመከፋፈሉ ዋና ምክንያት ብሔራዊ
ጥያቄ አልነበረም:: እንዲያውም ከአሥራዘጠነኛው ጉባዔ
የተጠበጠ (ፍርማል) መከፋፈል በኋላ ስለብሔራዊ ጥያቄ
የወጡትን የሁለቱን ወገኖች ፅብኔዎች ያመሳሰለ ሰው በቀ
ላሉ ሊገነዘብ እንደሚችለው፣ በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት
በክርክር ሊወገዱ የማይችል አይደለም:: የመከፋፈሉ ዋና
ምክንያት አዲስ ከገርቤት የወጡት ጉደቾ ከውጭ ማህበሮች
ይጠብቁ የነበሩትን "ዱርጆት" አለማግኘታቸው፣ በዚህ መበ
ሳጠታቸውና "የቀደሞዎቻችን" መታወም መጀመራቸው ነው::
ብሔራዊ ጥያቄ ለዚህ ተቃውሞ ጥሩ አጋጣሚ ሆኖ ተገኘ::
ሁለተኛ ነገር፣ እዚህ ላይ ማስታወስ የሚያስፈልገው ከጠ
ቀላላው ሁኔታ የተነሣ፣ በሁለቱም ወገኖች በኩል ስህተቶች
መደረጋቸውን ነው:: በተማሪ ማህበራት አቋምና ተግባር

ላይም ሆነ በብሔራዊ ጥያቄ ላይ የተደረጉት ክርክሮች ከክርክርም ይልቅ ንትርኮች ነበሩ:: የሉንዱ ጉዳዮች በታጠቁ ጽሑፎቻቸው "የርዕዮተ ዓለም ትግል ማሸነፊያ ዘዴ ያቸ" ተበላሽተው ነበር ቢሉ በእኔ አስተያየት ትክክለኞች ናቸው:: ለዚህም "መበላሸት" የመጀመሪያው ጎሳፊ ጥላሁን ታከለ ነው:: በዚህ ነገር ላይ እመለስበታለሁ:: ገን በሁለቱም ወገን ያሜሪካ ጉዳዮቻችን የነበረውን ሁኔታ ሐቀኛ ታሪክ ቢያወጡ ለተማሪ ማህበሮቻችን ብቻ ሳይሆን ለወደፊት ተራማጆች ሁሉ ትልቅ ትምህርትን እንደሚያተርፍ በዚህ አጋጣሚ ላሳስባቸው እወዳለሁ::

2. የኢትዮጵያ ተማሪዎችና ፊውዳላዊ ርዕዮተ ዓለም::

«የኢትዮጵያ ተማሪዎች በደፈናው የንኡስ ቡርዧው መደብ ክፍል ናቸው:: ስለሆነም የንኡስ ቡርዧው መደብ ጠባይ፣ የፖለቲካ አስተሳሰብና ርዕዮተ ዓለም አላቸው::»

«ውጭ አገር ያሉት የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራት ለውጭ ሰው የሚያሳዩት መልክ አንድ የተወሰነ ርዕዮተ ዓለም (ማርክሲስም—ሌኒንዝም) ያላቸው ድርጅቶች መልክ ነው:: እንደውነቱ ከሆነ ተንሠራርቶ የሚገኘው የንኡስ ቡርዧው ርዕዮተ ዓለም ነው:: የፊውዳል ርዕዮተ ዓለም ርዝራዥ በሰፊው አለ:: ከዚህም በላይ በፖለቲካ ዝንባሌ በኩል በቅርቡ የንኡስ ቡርዧ ሪቪስት ዝንባሌ ብቅ ብቅ ማለት ጀምሯል:: ነገር ግን አብዛኞች ማህበርተኞች ራሳቸውን



የሚያዩት በማርክሲስት—ሌኒንስት፣ ስለሆነና በየጉባዔው የሚያሳልፏቸው ውሳኔዎችና በየመጽሔቶች የሚወጡት ጽሑፎችም (የጥላሁን ታከለ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ነው!) የዚሁ ርዕዮተ ዓለም መግለጫ ስለሚመስሉ ለውጭ ሰው የተባበተ መልክ ይሰጣሉ::» . . . ገጽ 38 (ሁለተኛው ቅንፍ የተጨመረ)

«የፊውዳል ርዕዮተ ዓለም አሁንም በተማሪዎች ህሊና ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ አለው:: በኢትዮጵያ ህብረተሰብ የተንሠራፋው የፊውዳል ርዕዮተ ዓለም በመሆኑ በኢትዮጵያ ተማሪዎች ህሊና አሁንም ተጽእኖውን እንደጣለ ቢገኝ የሚደንቅ ነገር አይደለም:: የሚደንቀው "የግራ ክንፍ" በሚባለው ከፍተኛውን ሪቮሉሽናሪ ርዕዮተ ዓለም ተቀብሏል በሚባለው ወገን ያለው ተፅእኖ የቱ ያህል ትልቅ መሆኑ ነው::» ገጽ 46

የኢትዮጵያ ተማሪዎች፣ ርዕዮተ ዓለም ጉዳዮች በየትኛው እንደሚወሰኑት ለመቁረጥ በይጠንቱ የቱ፣ አይመስልም:: «እንደእውነቱ ከሆነ ተንሠራርቶ የሚገኘው የንኡስ ቡርዧው ርዕዮተ ዓለም ነው» ይሉና፣ አልፍ ብለው ደግሞ፣ «በኢትዮጵያ ህብረተሰብ የተንሠራፋው የፊውዳል ርዕዮተ ዓለም በመሆኑ በኢትዮጵያ ተማሪዎች ህሊና አሁንም ተፅእኖውን እንደጣለ ቢገኝ የሚያስደንቅ አይደለም::» ይሉናል:: ይሁን እንጂ ዞር ዞር የመጨረሻው ምርጫቸው ፊውዳላዊው ርዕዮተ ዓለም መሆኑን ከገጽ 36 እስከ መጨረሻው የተጻፈው ሁሉ ያመለክታል::

ይህ ፊውዳላዊ ርዕዮተዓለም በምን በምን እንደሚታይ
ጓደች ይገልጹልናል:: የመጀመሪያው ምስክሮት በነርሱ ጓ
ዶች ላይ ተነዝቷል የሚሉት ሀሜትና ወሬ ነው::
«ባለፉት ሁለት ዓመታት የሰላዊ፣ የአብዮታዊውን የፊ
ውዳል "ተማሪ ፖለቲከኛ"፣ የረብሹሽና ዋ—መብይ ምሁራን፣
የፊውዳል መደቡ ጥገኞች ሀሜት፣ አሽሙር፣ ስድብና ጥላቻ
ማውረኛ ከሆኑት ወገኖች የማህበረችን አበሎች በጥቅል
ወይም በገል ይገኙበታል:: [illegible] 37
በዚህ አነጋገር ከሄዱን መላ ኢትዮጵያ በልጃሪያ ጓዶች ዙሪያ
የምትሽከረከር ይመስላል:: ይህ ሁሉ ሰው ከሰላዩ እስከ
"ረብሹሽና ዋ—ብይ" ምሁሩ — እንደዚህ ጠምደ የያዛቸው
ምን ስላደረጉ ይሆን? የሆኖ ሆኖ፣ ይህ ሁሉ ህዝብ
«በቪላ ውስጥ ይኖራሉ»፣ «ሁሉም ትገሮች ናቸው»፣ «የትን
ራይ ትገርጊ ገንበር ሊከፍቱ ነው»...ዉዘ ተ ብሎ አምቶ
አቸዋል ይላሉ:: እኔ በበኩሌ የዚህ ዓይነቱ «ሀሜት» ቢሰ
ነዘርባቸው እስከዛሬ ስሜቼ አላውቅም ነበር:: ግን ይህ
ነገር ቢደረገም ኖሮ የጓዶቹ አቀራረብ — አሁን በጽሑፉ ቸው
የወሰዱት — ፈጽሞ ትክክል አይደለም::

አንደኛ ነገር፣ ከላይ የተጠቀሱትን ዓይነት «ሀሜቶች»
ማንም ይሁን ማን ቢያወራቸው እንደቁም ነገር ፈጽሞ ለመውሰድ
አይቻልም:: እንዲያው ለስሜታ፣ ለጊሬ፣ «ታምተናል» ብሎ
ለማውራት ካልሆነ:: እርግጥ የዚህ ዓይነቱ ርካሽ ሀሜት ተነ
ዝቶ ከሆነ አውሪው እራሱ ቂል ነው ማለት ነውና ቅሉ መብል



ነበረበት:: በቪላ ውስጥ መኖር — ያውም ብዙ ሆኖ — ረብሹ
ሽና ዋ ከሆኑን፣ የረቪትን ሥራ ከመሥራት አያግድም:: እንዲያ
ውም ሲጠቅም የሚችሉ ሁኔታዎች ሊኖሩት ይችላሉ:: ስለትውልዱ
በሄሪቸው ከሆነ ፣ ሌላው ቢቀር በትምህርት ቤት ጓደኖቻቸው አ
ማካይነት፣ ሙሉ አዲስ አበባ ስያውቅ የሚቀር አይመስለኝም::
ደግሞም፣ ያውርያውም ሆነ ያሚሪካ ማህበሮቻችን የበሄሮችን
ሙሉ መብት በይፋ በደገፈበት በሁኑ ወቅት ስለዚህ ጥያቄ ብዙም
የሚጠነቅ የ'ተማሪ ፖለቲከኛ' ወይም 'ረብሹሽና ዋ—ብይ ምሁር'
ያለ አይመስለኝም:: ምናልባት ትኛ ሀሜት እለ ከተባለ፣
''ገንበር ሊከፍቱ ነው'' የሚለው ሊሆን ይችላል:: ስለዚያውም
እንዴ አናርግልን ወልፈው ከወሙ በኋላ የሀይለሥላሴ፣ የጸሐፊን
ቶችና ያሚሪካን ኢምፔሪያሊዝም ሰላዮች እነርሱን እነርሱን መስ
ታተሳቸው አይቀርም ብዬ እገምታለሁ:: ሀሜቱ በዚህ አደጋ ላይ
ምን ሲጠም እንደሚችል አይታይም:: ለማንኛውም፣ ገንበር መስ
ራቱ ትክክለኛ ነው ብለው ከወኑ፣ ሀሜት ሊከለክላቸው አይችልም::

ሁለተኛ ነገር፣ የለም ይህ ሁሉ ሀሜት ''ዓላማ አለው''
አደጋ አለበት፣ ትኛ ነው ከተባለ፣ ያልሸሪያ ጓዶች የታመበትን
በታና ያማቸውን ሰው ስም ሞር በማስረጃ ጋር ማቅረብ ይገበ
ቸው ነበር:: ያለበለዚያ፣ በደፈናው በየበታው የማህበራትን የ
ቀደም መሪዎች ከህቀሱና ከጠቀሙ በኋላ፣ በማስረጃ ላይ ያልተመ
ሠረተ ክስ ማቅረባቸው፣ እራሳቸው ጓዶች በሚህንኑት የተነሱ
ሥራ መጠቀማቸው ነው::

ጓዶቹ እንዲህ ይላሉ:-
የና ማህበርና የማህበራችን አባሎች የሚያደርጉትን
ርእዮተአለማዊ ትግል በቀጥታ መንገድ መቋቋም ቢያቀ
ታቸው:በዝቀተኛና ርካሽ በሆነው የፊውዳል የፖለቲካ
ትግል ዘዴ በመጠቀም ሊያጠቁን መሞከራቸው ነው::
ይህንን አድሃሪና ወራዳ የፊውዳል ዘዴ የሳበአደር
ኩራትና ገበረገብነት ባልተለየው ሪቮሉሽናዊ ሀቀ
እን. ቋቋቅለን እንጂ አላማችን ከቶ አይዘነፍም::
ከጠር ዳዳ ፈጽሞ አናፈገፍግም::’ /ገጽ 39.
ስርዝ የተጠመረ/

እዚህ ላይ አንዳንድ ነገሮችን በጥብቅ ማስተዋል ያ
ስፈልጋል::አንደኛ ነገር:ጓዶቹ ስለ የትኛው ‘ርእዮተአለምዊ
ተግላቸው’ እንደሚያወሩ በግልጽ አይታይም::እኔ እስከማው
ቀው ድረስ ከነዚህ ጓዶቹ በታጠቀ:በትግላችን:በቻሌንጅ ወ
ይም በሌላ የተማሪ መጽሄቶች የቀረበ ጽሁፍ የለም::ቢኖ
ርም ከአዘጋጆች በስተቀር እነርሱ መጻፋቸውን የሚያውቅ
የለም::በለጥላሁን ታከለ ጽሁፍ ከሆነ:አባሎቻችን በጥቀል
ም ሆነ በነጠላ:በጽሁፍም ሆነ በቃል ‘ጥላሁን ታከለ እና
ነን’ የሚል መግለጫ አውጥተው አያውቁም::’/ገጽ 40/
ይላሉ::እርግጥ ያልጀሪያው ማህበር ሁለት ወኪሎች ባውሮፓ
ው ማህበር አስራአንደኛ ጉባኤ ላይ ተገኝተው በብሄራዊ
ጥያቄ ላይ ያላቸውን አስተያየት አቅርበዋል::በዚህ ሁኔታ
የትኛውን ርእዮተአለማዊ ትግላቸውን ‘በፊውዳል የፖለቲካ
ትግል ዘዴ’ ማን ሊቋቋማቸው እንደሞከረ ፈጽሞ አይታይም::



ሁለተኛ ነገር፣ እኚህ ጓዶች እዚህ ላይ ስለ ሳብአደር ኩራ
ትና ገበረገብነት’’ ያውሩ እንጂ በሌላ ቦታ ለሚስነዘርባቸው
ተንኮል ‘ጠርስ ትእግሥት’’ እንደሌላቸው ይናገራሉ::’’ይዘገ
ንነናል፣ ገን ምን እናደርጋለን!’’ ይላሉ:: ይህ ዛቻ መሆኑ
ግልጽ ነው:: በተጨማሪ፣ በዚህ ጽሁፋቸው ውስጥ የሚስነዝሩት
ሁሉ ተንኮል ’’ጠርስ ትዕግሥት’’ እንደሌላቸው ያሳያል:: ታዲ
ያስ፣ የሳብአደሩ ኩራትና ገበረገብነት የት ላይ ነው::

ሦስተኛ ነገር፣ በተለይ ሀሜትንና የሀሰት ወሬን በማሰወራት
በኩል፣ እነዚህ ጓዶች አሪብቸው ቢያንብ ተጠቅመውበታል፣ ይጠ
ቀሙበታል:: ለዚህ ’’ያይን ምስክሮችን’’ ለመጥቀስ ይቻላል::
በ1971፣ ከልጂሪያ ጓዶች አንዱ ለብዙ ወራት በስዊድን፣
በቤኒሉክስ፣ በጣሊያንና በሌሎችም ቦታዎች እየዞረ ያንዳንዱ
የቀደሞ የተማሪ ማህበሮችን መሪዎች ስም ሲያጠፋ ከርሞ እን
ደተመለሰ በተጠቀሱት አገሮች ያሉ ብዙ ጓዶች ይመሰክራሉ::
በተለይም ያንዳን ጓድ ስም እያነሣ ‘ፀረረቮሉሽናዊ ነው፣ አ
ደገኛ ነው፣ ተጠንቀቁ፣ ኩዴታ ለማድረግ ከሚፈልጉ ሰዎች ጋር
ይደልታል...ወዘተ’’ እያለ ሲለፍፍ እንደከረመ ብዙዎች ያው
ቃሉ:: ይህንን የጠቀስሁት የሀሜቱ ከንቱነት በመርሳት ባይ
ሆን፣ ያልጀሪያ ጓዶች የሀሜትን ጉዳይ ስለሚያነሱት ብቻ ነው::
ያልጀሪያ ጓዶች የዚህን የጓዳቸውን ሥራ ይስቱታል ብዬ አል
ገምትም:: ታዲያስ፣ ’በሸሳ ውስጥ ይኖራሉ’ ወይንም’’ ትገሩ
ዎች ናቸው’’ ከሚለው አሥር እጅ የበሰውን ይህንን ሀሜት ለምን
ባይጠቅሱት አለፉ ?

ሌላው ቀርቶ፣ አሁን በቅርብ የኤርትራ ተማሪዎች ጠቅላይ ማህበር ጉባዔውን ባደረገበት ወቅት፡ ያልጀሪያው ማህበር ወክሎ በይፋ "ያውሮፓን ማህበር መሪዎች አትመኑባቸው፣ እነርሱ ፀረረቮሉሽነሪውያን ናቸው ወዘተ" ብሎ መናገሩን የኤርትራ ጓዶች እራሳቸው ይመሰክራሉ:: በተረፈም፣ የብዙዎችን ጓዶች ስም በማጥፋት ወደአሜሪካ፣ ወደአውሮፓ አገሮች፣ ወደ ቅርብ ምሥራቅ ወደ ኢትዮጵያ በአልጄሪያ ጓዶች በየጊዜው በደብዳቤ የተነዛው ሀሰት ወሬ ሁሉ ያደባባይ ምስጢር ነው:: አሁን እንደሚገባው ከሆነ፣ በቅርብ እነዚህ ጓዶች የሚያሰራጩት መፈክር (ስሎጋን) "እኛ የሌለንበት ረቮሉሽን ሊደረግ ይችላል፣ እነርሱ ግን ያሉበት ምንም ረቮሉሽን አይደረግም" የሚል ነው:: ምናልባት ይህንን ሁሉ "ማንም ሰው ለቅርብ ጓደኛውና ጓዱ እንደልቡ፣ ባያወጣ ባያወርድ፣ የሆነ ያልሆነ ነገር፣ ሀሜት ያልተረጋገጠ ወሬ እንደሚያናፍስ ማንም አያውቅምን?" (ገጽ 41) በማለት የተንኮል ሥራ መሆኑን ለመካድ ይሞክሩ ይሆናል!::

ከዚህ በላይ እንዳልሁት፣ ያልጄሪያ ጓዶች በሚሉት መንገድ መታማታቸውን ስሰማ የመጀመሪያ ጊዜ ነው:: ሀሜቱ ቁምነገር የሌለበት ቢሆንም፣ ዘዴውን ግን በጥብቅ እቃወመዋለሁ:: የርእዮተዓለምና የፖለቲካ ትግል፣ አለመስማማት፣ አለመግባባት፣ መቃረን ካለ ይህ ሁሉ በግልጽና በደባባይ— በተለይም በመጽሔቶቻችን አማካይነት— መካሄድ አለበት:: ይሁን እንጂ ይህንን የተንኮል ዘዴ ከመጀመሪያውም፣ አሁንም በስራው አየተጠቀሙበት፣ ተጠቀሙበት ብለው ያልጀሪያ ጓዶች ሌሎችን ሲከሱ የራሳቸውን ሥራ ለመሸፈን የተነሡ ይመስላል:: ሌባን



ሌባ ቢሠርቀው እንዴት ይደንቀው እንደሚባለው ነው:: ያልጀሪያ ጓዶች በእውነት "በላብአደር ኩራትና ግብረገብነት" ፣ "በረቮሉሽናዊ ሐቀኝነት" የሚያምኑ፣ የሚመሩ ከሆነ፣ በሌሎች ላይ የሚያቀርቡትን "ሂስ" በራሳቸው መጀመር ነበረባቸው::

ይሁንናም በነዚህ ጓዶች አስተያየት፣ "በግራ ክንፍ ርእዮተዓለም ውስጥ የላብአደሩና የረቮሉሽነሪውያን ግብረገብነት ምንም ቦታ የሌለው መሆኑን" ባስዮአቸው ሁለት ሌሎች ነገሮች አንዱ የሠናይ ልኬ "ኢዞና በይማንገዝሲ" ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ያጭበረበረው <u>ቻሌንጅ</u> ጉዳይ ነው:: የመጀመሪያውን የሉንዱ ጓዶች የታጠቁ ጽሑፍ —ምንም እንኳ ያልጀሪያን ጓዶች ያስጠገበ ቢሆንም— ኮንኖታል:: የቀደሞው የቻሌንጅ አዘጋጅ ይህንን የሠናይን ጽሑፍ እንደሚቃወም በመግለጫ አስታውቆ ነበር:: ሥራው ያንዱ ሰው፣ የሠናይ ልኬ ሲሆን፣ ያልጀሪያ ጓዶች "የንኡስ ቡርዧ ፋሺስት መደብ" የሚለውን የተማሪ "ክፍል" የመሠረቱት በርሱ ላይ ነው::...ይሁንና፣ ማንኛውም ረቮሉሽናዊ ኢትዮጵያዊ የዚያን የሠናይ በይማንገዝሲ በደንብ እንደሚኮንነው ግልጽ ነው:: ስለዚህ፣ አሁን በርሱ ላይ እንደገና በዝርዝር አልመለስበትም::

በተለይ ላንባቢ ለማመልከት የምፈልገው፣ በጭበረበረው ቻሌንጅ ምክንያት በውሮፓ ማህበር አመራርና በጓድ መለስ አያሌው መካከል ተነሥቶ የነበረውን ውዝግብ ያልጀሪያ ጓዶች በዚህ ጽሑፋቸው ውስጥ <u>እንዴት እንደሚጠቀሙበት ነው</u>:: ከዚህ በላይ ለተጠቀሰው፣ በቀጥታ ጓዶችን ለሚመለከተው ለሠናይ ልኬ

ጸሁፍ ሁለት ገጽ ብቻ ቢበጡ፡ለዚህናው ግን አምስተ ገጽ
ሙሉ አውለውለታል፡፡ምክንያቱም "ጸረሪቮሉሽና ዊ የፊውዳል
'ገብረገብነት' በገራ ከንፋ ሀሊና ላይ ትልቅ ተጽእኖ
ያለው መሆኑን ወለል አድርጉ ያሳየን ከላይ የጠቀስነው
/የሰናይ ጉዳይ/ ሳይሆን" /ገጽ 42/ ይህናው የቻሌን
ጁ ጉዳይ ነውና፡፡ያኔ በጊዜው፡የዛሬ አመት፡ስለአጭበርባሪ
ው ቻሌንጁ ይዘትም ሆነ በጓዶች እሉህና መለስ መካከል
ስለተፈጠረው 'ጠብ' ያልደሪያ ጓዶች አንዳቸውም አስተያየት
አልሰጡም ነበር፡፡'ሌላ ማስረጃ እስከናገኝ ድረስ ዝም
ብለን ነበር'/42/ ይላሉ፡፡ከዚያ ወዲህ ሌላ 'ማስረጃ'
— የምን እንደሆነ አይታወቅም — አግኝተዋል ወይ፡፡ የለ
ም፡፡'አሁን ግን ጓድ እሉሁ ምንም አይነት የማስተባበያ
መግለጫ ወይም የግል ሂስ ጽሁፍ ሳያወጣ አስተያየታችን
ን መግለጽ የግድ ይሆንብናል፡፡'/42፡፡ሰርዝ የተጨመረ/
'አስተያየታቸውን' ለመስጠት ጓዶች የመረጡት ጊዜና ሁኔታ
— ጽሁፋቸው በ125ኛው ጉባኤ ላይ፡በጓድ እሉሁ ሊቀመንበ
ርነት በተሰበሰበ በዚህ ጉባኤ ላይ፡ሊቀርብ የታቀደ እን
ደነበረ እናስታውስ — በጣም ትርጉም ያለው ነው፡፡

እንደሚታወሰው፡በዚህ በአጭበርባሪው ቻሌንጁ ምክንያ
ት የተነሳው አለመግባባት፡በህዳር 1964 በወጣው ትግላች
ን/ቁጥር 3/ አማካኝነት ተዘግቷል፡፡ይህ ከሆነ፡ያልደሪያ
ጓዶች ይህንን የተዘጋ ጉዳይ፡ቢያንስ ቢያንስ አለመግባባቱ
ን በሚመለከተው በኩል የተቀበረ ንትርክ እንደገና፡እሬሳ
እንደሚያወጣ ጅብ ቆፍረው ለማውጣትና ነፍስ እንዲዘራ ለ
ማድረግ የተነሱበት ምክንያት ምንድነው፡፡የተጠቀሰው ትግላ
ችን ቁጥር 3 ባወጣው የመጨረሻ መግለጫ ጓድ እሉሁም፡ትግ



ላቸንም መሳሳታቸውን ካመኑ በኋላ ያጭበርባሪውን ቻሌ
ንጁ ሰሪዎች ሁሉም አበረው እንዲፈልጉ ጥሪ ያደርጋል፡፡
እርግጥ፡በጓድ እሉሁና በትግላችን የተደረጉት ስህተቶች
ፍጹም አሳፋሪ ነበሩ፡፡እርግጥ፡ይህ የጠቀስኩት የትግላች
ን የመጨረሻ መግለጫም በኔ አስተያየት ፍጹም በቂ አልነ
በረም፡፡ግን በጠቅላላው ስህተቱ ከማን እንደሆነ ታውቋል፡፡
የተሳሳቱት ጓዶችም በግልጽ መሳሳታቸውን አምነዋል፡፡በዚህ
በኩል ጉዳዩም እንደተዘጋ ተቆጥሮአል፡፡

ያልደሪያ ጓዶች አሁን፡በተባለው ጊዜና ሁኔታ፡ነገ
ሩን ማንሳታቸው ለሁለት ግብ ነው፡፡ የመጀመሪያው፡በተለይ
ጓድ እሉሁን ለማሳጣትና በጠቅላላውም ባውሮጳው ማህበር አ
መራርና በጓድ መለስ መካከል ተነስቶ የነበረውን 'ጠብ'
እንደገና በማፋፋም ሁለቱን ወገኖች ለመለያየት ነው፡፡እ
ንዲቆራረጡ ለማድረግ ነው፡፡እንዲያውም በዚህ የጽሁፍ ክ
ፍል መጨረሻ ላይ ለጓድ መለስ የሚያቀርቡት ሀሳብ 'የመ
ጨረሻ መቆራረጥን' ነው፡፡

'የበላይ ስራ ትሰራለህ ብሎ መጠርጠር ወይም በተደ
ብቅ ስራ ትኩፋፍላለህ ማለት ግን መልሱ የመጨረሻ መቆራረ
ጥ ነው፡፡ ...' /ገጽ 47/

በኔ አስተያየት፡የመጨረሻው 'ወራዳው ተንኮል' እንደ
ዚህ ነው፡፡አንባቢ ያስተውል፡፡ያልደሪያ ጓዶች ጓድ እሉሁ
የግል ሂስ እንዲያቀርብ፡ወይንም ትግላችን ያወጣው መግለጫ
በቂ ስላልሆነ ሌላ የተሻለ እንዲያወጣ፡ሁለቱም ወገኖች ሂ
ስና የግል ሂስ እንዲያደርጉ የበለጠ መግባባት እንዲ
ፈጠር አይደለም የሚጠይቁት፡፡መቆራረጥ እንዲመጣ ነው፡፡

ሁለተኛው ገባቸው ደግሞ፡ጌዱ መለሰን የድገፉ መስለ
ው ሁለቱንም ወገኖች በተማሪዎቻቸና በተራማጆቹ ሁሉ ዘንድ
አሳጥተው፡ደምሰሰው የራሳቸውን ሀቁና 'ሪቮሉሽናዊነት'
ቦግ አድርጎ ለማሳየት ነው፡፡በጌዱ አልሁና በትግላችን
በኩል የተደረገው ስህተት፡ስህተት ባይሆን ታስቦበት፡በእው
ቀ የተከናወነ 'ወራዳ ተንኮል'፡'ወራዳ ተግባር' መሆኑ
ን ለማሳመን የባጡን የቆጡን ያወርዱና 'ጌዶች እየተባባሉ
በአንድ እጃቸው አንገት ለአንገት ተያይዘው እየተሳሳሙ
በሌላው እጃቸው በየእርስ በርሳቸው ጀርባ ላይ ጩቤ የሚ
ሰኩት የፊውዳል መሳፍንት ናቸው፡፡/ገጽ 47/ ቢሉ እነጌ
ዱ መለሰና እልሁ፡እንዲሁም 'የቀድሞዎቻቸ' የተባሉት ሁሉ፡ከተ
ባለው 'የፊውዳል ርእዩተአለም' ገና ያላመለጡ፡ያልጀሪያ
ጌዶች ግን በንጹህ 'የላብአደር ግብረገብነት' የሚመሩ መሆ
ናቸውን ሊያሳምኑ ይጣጣራሉ፡፡በእውነቱ ግን ይህ ስራቸው
ከላብአደር አቋምና አሰራር ጋር ፈጽሞ የማይዛመድ መሆኑን
ማንም እንደሚረዳው እምናለሁ፡፡

ያልጀሪያ ጌዶች በገራ ከንፉ ላይ ያለውን 'ፊውዳል
ርእዩተአለም' ለማሳየት ሌሎች ምሳሌዎቻችን ያቀርባሉ፡፡አ
ንዱ ምሳሌ፡ገራከንፉ በፍልስፍናና በህብረተሰባዊ ሀሳቡ
/ሶሻል አይዲያስ—ሶሻል ቫሊውስ/ የፊውዳል ርእዩተአለም
ን ተጽእኖ ማሳየቱ ነው፡፡ይህ በምን በምን ታያቸው፡፡

ሀ/ የመጀመሪያው፡በጥላሁን ታከለ ጽሁፍ ውስጥ ያሚ
ሪካ ጌዶች 'ሶሻልሾቪኒስቲስ' መባላቸውና ይህም በገራ
ከንፉ ዘንድ 'ክብር' እንደመንካት መቆጠሩ ነው፡፡
'በፊውዳል አስተሳሰብ አንድ ሰው 'አዋቂ' የሚባለው
በደፈናው ስለሆነ ሁሉን ነገር የሚያውቅ ያስመስለዋል፡፡



ስለዚህም በምንም ነገር/ተራም ነገር ቢሆን/ አዋቂ አለመ
ሆኑ በህዝቡ ፊት፡ባደባባይ ከታየ ጠቅላላ እውቀቱ የተሻ
ረ ይመስል ተዋረደ ማለት ነው፡፡...'ይላሉ ያልጀሪያ
ጌዶች/ገጽ 48/

በፊውዳል ህብረተሰብም ውስጥ በመጠኑ የስራ መከፋፈ
ል አለ፡፡'መድሃኒት አዋቂ'፡'የጂ ጥበብ አዋቂ'፡'ነገ
ር አዋቂ'... ይባላል፡፡'በደፈናው' የሚለው ልክ አይደለ
ም፡፡ይሁን እንጂ አሁን በርሱ ላይ አልከራከርም፡፡

ከዚህ በላይ እንደተመለከተው፡የጥላሁን ታከለ ጽሁ
ፍ ባቀራረቡ የተባሉትን ጌዶች ያስተሳሰብ ስህተት ለማሳ
የት ብቻ ሳይሆን፡ወይንም ስለብሄራዊ ጥያቄ 'አለማወቃቸውን'
ለማሳየት ብቻ ሳይሆን ጌዶችን ሙሉ በሙሉ ለመደምሰስ፡ፈ
ጽሞ ከተማሪ ማህበራት እንዲነጠሉ ለማድረግ የተሰራ
ነበር፡፡ጽሁፉ የተባሉትን ጌዶች 'ሶሻልሾቪኒስቶች' ብሎ
መሰየሙ የዚህ የመደምሰሻ ትርጓሜ አንዱ፡የሁለተኛ ደረጃው
ጎኑ ነው፡፡ስለዚህም፡ያልጀሪያ ጌዶች፡ይህችን ብቻ ከዚያ
ካልታሰበበት፡ጊዜንና ቦታን ከማይለይ ገለበጣ አውጥተው
ማቅረባቸውና በዚህ አማካይነት በገራከንፉ ሀሳብ ላይ ያ
ለውን 'የፊውዳል ርእዩተአለም' ተጽእኖ 'ለማሳየት' መሞ
ከራቸው በይፋ ለማጭበርበር መቃጣት ነው፡፡የጥላሁን ታከለ
ጽሁፍ በማህበሮቻችን ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ፡እንኳንስ በ
በተማሪ ማህበራት ቀርቶ በሪቮሉሽናዊ ድርጅቶችም ውስጥ
ቢሆን ዛሬ በታላቅ ጥንቃቄ ብቻ የሚሰራበትን የሂስ ዘዴ
ያለቦታው በማምጣቱ መኮነን እንዳለበት ለመሸሸግ መሞከራቸ
ው ነው፡፡

ይሁን እንጂ፡ የተባለው ግራ ክንፍ እኔ እስከማውቀው
ድረስ ስለጥላሁን ታከለ ጽሁፍ በግልጽ ያቀረበው ደንበኛ
ሂስ የለም፡፡ምናልባት ያልጸሪያ ጓዶች የሚጠቁሙበት በታ
ጠቀ የወጣውን የሉንድ ጓዶች ጽሁፍ ሳይሆን አይቀርም፡፡
ይህ ጽሁፍ በተቃጣቢነቱ የሚመስገን ቢሆን፡ስለጥላሁን ታከ
ለ ጽሁፍ የሚለው 'የርእዮተአለም ትግል ዘዴ' ማበላሸቱ
ን ነው፡፡ይህንን በሳለም፡ያልጸሪያ ጓዶች እንደሚሉት የ
ነ'ጠንበን በበር' ነከተሰለ፡'አቋርጧቸዋል'ማለቱ እንዳ
ይደለ ግልጽ ነው፡፡በየገጹ ላይ ማርክሲዝም–ሌኒንዝምን
የጠቃቀሰው ጥላሁን ታከለ በማርክሲስት –ሌኒንስት የትንተ
ና ዘዴ ቢጠቀም ኖሮ ቀጥታ ገለበጣን አያደርግም ነበር፡፡
በማርክሲዝም–ሌኒንዝም 'የገፋ' ቢሆን ኖሮ ከዚህ በታች
የምጠቀሰውን የማስተቢቶንግን ትምህርት ባስታወስና ትንሸ
ቀም በሉ ባሰላሰለበት ነበር፡፡

"... Our aim is exposing errors and criticising shortcomings,like that of a doctor curing a sickness,is solely to save the patient and not doctor him to death.A person with appendicitis is saved when the surgeon removes his appendix. So long as a person who has made mistakes does not hide his sickness for fear of treatment or persist in his mistakes until he is beyound cure, so long as he honestly and sincerely



wishes to be cured and to mend his ways,we should welcome him and cure his sickness so that he can become a good comrade. We can never succeed if we just let ourselves go and lash out at him. In treating an ideological or a political malady, one must never be rough and rash but must adopt the approach of " curing the sickness to save the patient", which is the only correct and effective method." ( Rectify the Party's style of work. ስርዝ የተጨመረ )

ለዚያውም ይህ የተባለው ፓርቲ ውስጥ ላሉ – ማለት
በአይዲዮሎጂያዊና በፖለቲካዊ ህሊና ቸው ከፍ ላሉት፡ግለሰ
በኝነትን በመጠኑ ላሸነፉት – የፓርቲ አባሎች መሆኑ እ
ንባቢ ያስታውሰው፡፡ጥላሁን ታከለ በጥራዝነጠቅነቱ በቀጥታ
ከሌኒን የወሰደው ገለበጣ ጓዶችን 'በህክምና የሚገድል':
'ያለ ቀጠባ/በጓዶች ላይ/ የሚወርድ ገፍታሪና ቸኳይ'የቁ
በትር መሆኑን ማንም ህቁኛ ተራማጅ አይስተውም፡፡ገና አ
ፉን ከመክፈቱ 'ሂሱ' የቀረበባቸውን ጓዶች የሚያቀከብ፡
'መታመሚ አለመታመማቸውን' እንኳን ጊዜና ፋታ የማይሰጣቸ
ው፡ፈጽሞ መተንፈሻ የማይሰጥ፡ዘሉ የሚያገቁ 'ሂስ' ነው፡፡
እንግዲህ የተባለው 'የግራ ክንፍ'፡ያውም በጣም በተቀጠበ
አኳኋን፡ይህ አቀራረብ ትክክለኛ አለመሆኑን ስላመለከተ፡
ይህ 'የግራ ክንፍ' በፊውዳል ርእዮተአለም ተጽእኖ ስር የ
ሚኖር፡እነርሱና ጥላሁን ታከለ ግን 'ላበአደር ሪቮሉሽናዊ
ያን' መሆናቸውን ያልጸሪያ ጓዶች በዚህ በጽሁፋቸው ሊያሳ
ምኑን ይሞክራሉ፡፡ይህ ገብዝነት ነው፡፡

ግን ደግሞ እስቲ ከጥላሁን ታከለና ካሶደሪያ ሰዶች
በስተቀር መላው የኢትዮጵያ ግራክንፍ በፊውዳል አስተሳሰ
ብ ስር የሚኖር ነው እንበል::ይህ የፊውዳል ርእዮተአለም
ስለተጫነው ማንኛውም ሂስ ቢቀርብበትና ስላዋቂነቱ 'ባደ
ባባይ' ቢታይ የተዋረደ ይመስለዋል እንበል::በዚህ ሁኔታ
ያንዱ እውነተኛ ማርክሲስት-ሌኒንስት አቀራረብ ምን መሆ
ን አለበት::የተባለው የግራክንፍ 'የግራ' ነው ከተባለ:
ሌላው ቢቀር ጸረፊውዳልና ጸረኢምፔሪያሊስት አቋም አለው
ከተባለ:የማርክሲስት-ሌኒንስቱ ጓዱ ተግባር:የግራክንፉን
ጓዱ ሁሉ ቀስ በቀስና በትእግስት እያስተማረ ከፊውዳል
አስተሳሰብ ማውጣት:ለሪቮሉሽኑ እንዲሰለፍ ማድረግ ነው እ
ንጂ:የመደብ ጠላት ሆኖ በግልጸ እስኪለወጡ ድረስ:ቀንዱ
ቀንዱን እያሉ ማራቅ አይደለም::ይህ ነው ትክክለኛው አ
ቀራረብ::ስለዚህም:በኔ አስተያየት:ያሶደሪያ ጓዶችና ሌሎ
ችም ጥላሁን ታከለያች ይህንን እውነት እስኪገነዘቡት
ድረስና አቀራረባቸውን እስከሳረሙ ድረስ:ስለራባቸው 'ት
ክክለኛነትና' በለቀረው የግራክንፍ ሁሉ 'ስህተተኛነት'
በገበዝነትና በማመን የቂል በትራቸውን በየአቅጣጫው መሰ
ንዘር እስከሳቆሙ ድረስ የምላስ ሪቮሉሽናዊያን ብቻ ሁነው
ይቀራሉ::ይህ ብቻ ባይሆን:በጉረኛነታቸውና በቀስቃሽ/ኘሮ
ቮካቴ/ በራቸው በጠቀላላው የግራ እንቅስቃሴና የተማሪ
ማህበራት ላይወሰን የሌለው ጉዳት ያደርሳሉ::

ለ/ 'የፊውዳል ፍልስፍና የእውቀትንና የጸጋን
/ሺር ቹ/ መጠን የሚለካበት መሳሪያ አንዱ ገለ
ሰብ በሚሰራው ባይሆን በእድሜው ነው::' ገጸ 48

በሚከበሩት የግራ ክንፍ ላይ 'ከፍተኛ' የፊውዳል



ርእዮተአለም ተጽእኖ እንዳለ በማንኛውም መንገድ 'ለማረጋገ
ጥ'ሲሉ:ያሶደሪያ ጓዶች የሆነ ያልሆነውን ይዘባርቃሉ::ም
ን የመሳሰሉ ቴዎሪዎችን ሊሆን በማይችል መሰረት ላይ ይገ
ነባሉ::'እውቀትንና ጸጋን'ከእድሜ ጋር የሚያያይዘው 'የ
ፊውዳል ፍልስፍና' ባይሆን በፈረንጆች አነጋገር 'ህዝባዊ
ጥበብ'/ፖፑላር ዊዝደም/ የሚባለው:ምንም ያህል ባይለወ
ጥ ከትውልድ ወደትውልድ የሚተላለፍ 'ትምህርት' ነው::
ይህም ህብረተሰቦች ከተፈጠሩ ጀምሮ:ለወደፊትም ለረጅም
ጊዜ የሚቀይ ነገር ነው::በህዝባዊ ጥበብ እድሜ 'ከእው
ቀትና ከጸጋ' ጋር መያያዙ ላንዱ ማቴሪያሊስት ፈጽሞ የሚ
ያስደንቅ አይደለም::የህብረተሰብን ማቴሪያላዊ መኖሪያ
የሚፈጥረው በመሰረቱ 'ለእቅመ አዳም' የደረሰው የህብረተ
ሰቡ ክፍል ነው::በእድሜ 'የገፋ'ሰው'ብዙ ያየ' ነው::
የሰራና የኖሮ ልምድ ያለው ነው::ከህይወት ከራሷ የተማ
ረ ነው::ስለዚህም የሚቀጥለውን ትውልድ እንዲያስተምር
ይጠበቃል::

ይሁን እንጂ:ህዝባዊ ጥበብ ለገፉ እድሜ የሚሰጠው
ን የ'እውቀትና ጸጋ' መጠን ያህል:ባንዱ በኩል:ለወጣት
እድሜ ሌሎችን:ለህብረተሰቡ ያንኑ ያህል አስፈላጊ የሆኑ
ትን 'ጸጋዎች' — ድፍረትን:ቆራጥነትን:ታታሪነትን:'እ
ይዲያሊዝምን':...ወዘተ. — ይሰጣል::በሌላ በኩል ደግ
ሞ እድሜን ራሱን ይቃረነዋል::

ህዝባዊ ጥበብ የሚገለጸው በተረቶችና ምሳሌያች:ሰፊ
ው ህዝብ እንደየሁኔታው አስተያየቱን ለማብራራት በሚጠቃ
ቀሳቸው 'ያባቶች' ንግግር ነው::ደግሞም በርግጥ ጥበብ
ነው::ጥልቅ ነው::ግን 'እንደየሁኔታው' ስለሆነና ህይወ

ቶም እራሷ የቀራኒያች አንድነት ስለሆነች፡ ተረቶችና ምሳሌያች ለብቻቸው ተነጥለው ከታቹ እርስ በርስ ይቃረናሉ:: ለዚህ ሁሉ ብዙ ምሳሌያችን ለማምጣት ይቻላል::

ጉልማሳ ከቆለበት ከበት አይ ነጠቅ፤
ሸማግሌ ተቆለበት ነገር አይወድቅ::

ግን ደግሞ:-

ያረጀ:ያፈጀ::ወይንም በስተርጀና ምንኩስና::ወ
ይንም ሸማግሌ ካልሞተ:ስንዴ ካልመረተ::...

'ሰውን ውደደው እንጅ አትመነው' የሚለው:ጓደች የጠቀሱት ምሳሌ ራሱ ቀራኒን ይዟል::ካሳመኑ እንዴት ለመ ውደድ ይቻላል::/ደግሞም:-'ሰውን አመነው እንጂ አትውደ ደው' ብሎ ተገልብጦ ይነገራል::ይሁንናም:ይህንን የግለ ሰበኝነት /ኢንዲቪጁዋሊዝምን/ ፍልስፍና — በነገራችን ላ ይ ይህ የካፒታሊስት ህብረተሰብ የፍልስፍና መሰረት መሆኑ የታወቀ ነው — የሚሰብከው ህዝብ በሌላ ቦታና ሁኔታ ደግ ሞ:'ምንም ቢያጥር ገመድ:ምንም ቢከፋ ዘመድ':'ድር ቢ ያብር አንበሳ ያስር':ጉረቤት ቢታማ ለኔ ብለህ ስማ': ... ወዘተ. እያለ መተጋገዝን:መተባበርን:ለርስበርስ መቆምን ... ይሰብካል::

ጠ/ ያልጄሪያ ጓደች 'የፊውዳል ፍልስፍና' ነው ብለው ስለ<u>ወዳጅነት</u> ስለ'ጓደኝነት':ስለ'መተማመን':ባደባ ባይ 'እቃ' ስለመውሰድና ስለአማርኛ ቋንቋ ስለራሱ:በሚያ ስደንቅ 'የስነጸሁፍ' ቋንቋ የሚጉነጉኑት ቴወሪ በጠቀላላው በየትኛውም ህብረተሰብ ውስጥ በሚገኙ:በሞላጉደል ከህዝባዊ ጥበብ በፈለቁ አስተያየቶች ላይ የተመሰረተ ነው::በተረቶ



ችና ምሳሌያች መጠቀም አያስፈልግም ማለቴ አይደለም::ወ ይንም ደግሞ ያንድ ህዝብ ቋንቋ የህዝቡን ባህልና ልምድ — ከዚያም አልፎ የህዝቡን የማቴሪያላዊ ስልጣኔ ደረጃ — አያንጸባርቅም ማለቴ አይደለም::ነገር ግን በተረቶችና ም ሳሌያች መጠቀም አንድ ነገር ነው::የእነዚህን ተረቶችና ምሳሌያች አንድ ጉን ብቻ ወስዶ እንደአንድ ህብረተሰብ 'ፍልስፍናዎች' ማቅረቡ ደግሞ ሌላ ነገር ነው::ያልጄሪያ ጓደች የሚያደርጉት ይህንኛውን ሁለተኛውን ነው::በገራብ ጉፉ ላይ 'የፊውዳልርእዮተአለም' አለበት ካሉ በኋላ:ከገ ራብጉፉ የመደብ አመጣጥ ወይንም ከማቴሪያላዊ እቋሙ ተነ ስተው ይህንን በማሳየት ፈንታ ተረቶችንና ምሳሌያችን እ ንደማስረጃ አድርገው ያቀርባሉ::ይህም በቡርዧ ሶሲዮሎጅ ስቶች አምሳያ:የህብረተሰቡ 'የላይ ግንብ'/ሱፐርስትረክቸ ር/ ከሚገባው በላይ:ከመሰረቱ/ከቤዙ/ የበለጠ ዋናነት መ ስጠት ነው::የስያችንና የመደቦችን እቋም የሚወስነው ይህ ው 'የላይ ግንብ' ነው እንደማለት ነው::ያልጄሪያ ጓደች ይህንን አስተሳሰብ ወስደው 'በኢትዮጵያ ደጋያች ለሺህ አ መታት ያህል የደረጀው'ፊውዳሊዝም/ገጽ 50/ የፈጠረውን ርእዮተአለም ጠንካራነት ሲገልጹ የሚስማማ ሰው መቼውንም ቢሆን በኢትዮጵያ ሪቮሉሽን ይደረጋ' ብሎ ማመን ያዳግተዋ ል::በዚህ አንጻር 'የቀድሞቷ ሩሲያ'ና የ'ሰበት ሺህ አ መታት' ፊውዳሊዝም የነበራት ቻይና ሪቮሉሽን ለማድረግ መ ቻላቸው እንደተአምር ሊታይ ነው ማለት ነው::

ስለቡርዧ ሶሲዮሎጅ ካነሳን ወዲያ:ጓደች የፊውዳል ርእዮተአለም መግለጫ ብለው የሚደረድሩትንና ካማርኛ ቋንቋ ም ጋር የሚያያይዙትን ቴዎሪ ከዚህ በታች ለሸይን የተባለ ሰው ከሚለው ጋር ማመሳሰል ይጠቅማል:-

"Oral sadism is further manifest among the Amhara by the nature of their speech.The Amhara are not only loquacious but also tend, both in manner of delivery and in content of conversation to be biting and intrusive. Backbitig, insulting arguing, and litigating are among their more characteristic modes of self-expression. . . . Ambiguous language and obscure allusion make possible a good deal of socially admissible, and admired insulting. Just as the Amhara tends to be tight-lipped and evasive when confronted by questions he does not feel like answering, so he finds pleasure in stubbornly withholding his meaning from his audience through employing figures and allusions which no one can understand...." ( D.N. Levine. Wax and Gold 1965 pp. 229 - 230)

ለቪይን ያማራ ህዝብ ባህርዮች ብሎ የሚያቀርባቸው ን በተቃርኖ የቆሙ ፈጠራዎች ያለደሪያ ጓዶች ወደ 'ፈውዳል ፍልስፍና' ለውጠውታል::እርሱ እንደ ባይክሎፒያዊ በሽታ — ኦራል ሳዲዝም — የሚመለከታቸውን 'ጠባዮች እነርሱ እንደፈውዳል ርእዮተአለም 'ተጽእኖ' ያቀርቡታል::ጓዶች በዘመናዊው የቡርዧ ሳይኮአናሊስስ ጫካ ውስጥ ገብተው መንገዱ የጠፋባቸው ይመስላል::ትንሽ ቆይተው 'እንወራረድ: እሺ ያ እንረድ:እኔ ጠባሸ አንተ ቀማሸ' የሚለውንም የፈውዳል ፍልስፍና ነው ይሉን ይሆናል::

ያለደሪያ ጓዶች ይህንን ሁሉ ውጥንቅጥ ወሬ የሚያወሩት:ባንድ በኩል ጥላሁን ታከለ ባያሰበበት ያደረገው ገልብጣ በተማሪ ማህበሮቻችን ውስጥ ያመጣውን ፈጸሞ የማይገባ ያከራከር ዘዴ — የቤኔሉክስ ጓዶች ባለፈው አመት ታጠቀን ለማሳጣት የተጠቀሙበትን:እንጂህ ጓዶች ራሳቸው በዚህ ጽሁፋቸው ውስጥ የሚጠቀሙበትን:እኔም እራሴ በመጠኑ አሁን እንደጠቀምበት የተገደዱሁትን — ለመሸፈንና:በሌላ በኩል ደግሞ:በዚህ ጽሁፍ መጀመሪያ ላይ እንደተባለው:የነርሱን 'ንጽህ ሪፐሉሽናዊነት' ለማሳየት ነው::'የተማሪዎች ማህበሮቻችን የግራክንፉ ሳይቀር ከፈውዳል ርእዮተአለም ሙሉ በሙሉ ያልነጹ ናቸው::'ና::/ገጽ 53/

## 3. ያውሮፓው ማህበርና ዲሞክራሲ

ያለደሪያ ጓዶች ያውሮፓውን ማህበራችንን የተጨበጠ ሁኔታ ወይ አውቀው ይረሱታል:ወይንም አውቀው ያጣምሙታል:: በሌላ አነጋገር:የማህበሩን ሁኔታ ከተጨበጡ ሀቆች ተነስተው በመመርመር ፈንታ:ግለሰባዊ/ሰብጀክቲቭ/ በሆነ መንገድ አንዳንድ ፍርዶችንና ግምቶችን በማቅረብ እውነቱን አጣምመው ለክርክራቸውና ገና በገልጸ ሳልተናገሩት አሳማቸው ያውሉታል::

. . . እስከቅርብ ጊዜ ድረስ ማህበሮችን የመሩት ሰዎች/አወቁትም አላወቁትም/ ማህበሮችን የመሩት እንደአንድ የፖለቲካ ፓርቲ/አንድ ርእዮተአለም: ጥብቅ ዲሲፕሊን እንዳለው ፓርቲ/ ወይም እንደአንድ ፓርቲ የተማሪ ቅርንጫፍ አድርገው ነው::ይህም የሚታየው መሪዎች በአብዛኛው ተማሪ ላይ በነበራቸው ከፍተኛ ጥርጣሬና ፍርሃት /አድሃሪ ነው' በሚል ሰበብ/:እንዲሁም ብዙ ሁኖ መጥቶ ከሰልጣን እንዳያወርዳቸው /እነሱ 'ማህበሩ አድሃሪ እንዳይሆን ይላሉ/ በነበራቸው ፍርሃት ምክንያት:የነ

ርሱን ርእዮተአለምና የፖለቲካ ዝንባሌ ያልተቀበለው
ን ሁሉ ባጠቃላይ 'አድሃሪ' በማለት አበዛኛውን ተ
ማሪ ከማህበሮቹ ውጭ እንዲሆን በማድረጋቸው ነው::
ስለዚህም ነው:በውጭ አገር ያሉት ማህበራት በአንድ
በኩል የምርጥ ሰዎች 'ህብረሰባዊ ክበብ' የሚመስሉት::
አንድ ህዝባዊ ድርጅት ሊቀበላቸው ከሚገባው አባሎች
ሩቡን ያህል እንኳን ሳይጠቀልል እንዴት ተብሎ ህዝባ
ዊ ድርጅት ይሆናል::በአውሮፓ 1000 ያህል ተማሪዎ
ች:በአሜሪካ ከሁለት ሺህ በላይ ተማሪዎች አሉ·ይባላ
ል::የያንዳንዱ ማህበር አባሎች ግን ከሁለት መቶ አ
ይበልጡም::/ገጽ 29. ሰርዝ የተጨመረ/

በዚህ አነጋገር መሰረት:በውጭ አገር ያሉት የኢትዮ
ጵያ ተማሪዎች በበዛት ማህበርተኛ ያልሆኑት በመሪዎቹ ጥፋ
ት ነው::መሪዎቹ ተማሪን 'አድሃሪ' እያሉ ስላባረሩት
ነው::'ከስልጣን እንዳያወርዳቸው' — ከየትኛው 'ስልጣን'
ጌዶች — በመፍራታቸው ነው::...ወዘተ.

አይዲያሊስት የጥያቄ አጠናን ማለት እንደዚህ ያለው
ነው::የተጨበጠው:ህያውና የተማሪ ማህበራት ሁኔታ ግን አ
ንዴት ነበር ብንል ፍጹም የተለየ መልስ ይገኛል::ከተጨ
በጠው ሁኔታ በመነሳት በመጠኑ የማውቀውን ያውሮፓውን ማ
ህበር ታሪክ ትንሽ ልዘርዝር::

ያውሮፓው ማህበር ሲፈጠር አላማው የሃይለስላሴን መ
ንግስት ፕሮፓጋንዳ በውጭ አገር — በተለይም በአውሮፓ —
ለማስፋፋት ነበር::ስለዚህም ከሃይለስላሴ መንግስት እስከ
1965 ድረስ በያመቱ አስር ሺህ የኢትዮጵያ ብር ይሰጠው



ነበር::እንደዚሁም እስከ 1966 መጨረሻ ድረስ ሃይለስላ
ሴ የማህበሩ 'የበላይ ጠባቂ' መሆኑ በግልጽ — በማህበሩ
የደብዳቤ መጻፊያ ወረቀቶች ላይ በተለይ — ይጠቀስ ነበ
ር:: እስከ 1960 ገደማ ማህበሩ የለ
ሰለሰ ጥገና/ሪፎርም/ ፖለቲካ ነበረው::ከሃይለስላሴ የሚ
ሰጠው ገንዘብና በዚህ በለሰለሰ ፖለቲካው ምክንያት:ማህ
በሩ ከተፈጠረ እስከ 1965 ድረስ:ባውሮፓ የሚገኘው ተ
ማሪ ሁሉ ማህበርተኛ ነበር::'ማህበርተኛ' ነበር ሲባልም
ባመት አንድ ጊዜ የሚደረገው ጠቅላላ ስብሰባ ላይ ይገኝ
ነበር ማለት ነው እንጂ ባመቱ ውስጥ አንዳቸም በማህበሩ
ውስጥ የሚከናወን ስራ አልነበረም::

በ1965 በቪየና በተደረገው ጉባኤ ላይ ማህበሩ ለ
መጀመሪያ ጊዜ የጥገና ፖለቲካውን ወዲያ ጥሎ 'ፊውዳሊዝም
ና ኢምፔሪያሊዝም ይውደሙ' የሚል ሰንደቅ ይዞ ተነሳ::
ይህም በማህበሩ ህይወት ውስጥ ከፍተኛ ለውጥ ነበር::በሚ
ቀጥለው አመት:በእንግሊዝ አገር በተደረገው ጠቅላላ ስብ
ሰባ ላይ የሃይለስላሴ መንግስት የተለመደውን አስር ሺህ
ብር ከለከለ::ከዚሁ ጸረፊውዳልና ጸረኢምፔሪያሊስት
የፖለቲካ መስመር የተነሳ:በዚያውም ከሃይለስላሴ መንግስት
ና ከማህበሩ መራራቅ የተነሳ:ቀደም ከሁለት መቶ በላይ ሁ
ኖ ይሰበሰብ የነበረው ተማሪ በንግሊዝ አገሩ ስብሰባ ላይ
በግማሽ ተቀነሰ::የተሰበሰበው ወደመቶ ገደማ ነበር::የተ
ሰበሰበው ቁጥር እንደማህበሩ ጥንካሬ መለኪያ ከተወሰደ:
ከ1966ቱ ጠቅላላ ስብሰባ ወዲህ ይህ ቁጥር በ120 እና
በ150 መካከል ሆኖ ስለሚገኝ ጥንካሬው ምንም ያህል አል
ተለወጠም ለማለት ይቻላል::ለማንኛውም:የመጀመሪያውና ዋናው

የማህበርተኛ ቁጥር ቀናሽ የማህበሩ ግልጽ ጸረፊውዳልና ጸ
ረኢምፔሪያሊስት ስም እንደነበረ ግልጽ ነው::ሁለተኛው
የቁጥር ቀናሽ — ያውም ቀናሹ ምንም ያህል አልነበረም —
በ1967ቱ ጉባኤ ላይ ማህበሩ በግልጽ የህዝባዊ ዲሞክራሲ
ሪቮሉሽንን አስፈላጊነት ይዞ መውጣቱ ነው::ባጭሩ:ከ1965
በፊት ባውሮፓ የሚገኝ ተማሪ ሁሉ ማህበርተኛ ነበር::ከዚ
ያ ወዲህ ግን ከፖለቲካ መስመሩ የተነሳ ከግማሽ በላይ ·ማ
ህበርተኞች ጥለውት ሄደዋል::እንግዲህ መቸስ እነዚህ ሁለ
ት የእድገት ደረጃዎች መድረስ አይገባቸውም ነበር ለማለት
አይቻልም::

·ማህበርተኞችን የመሩት እንደአንዱ የፖለቲካ ፓርቲ
... ወዘተ.· የተባለው ሀቁና ክሪቲክ አይደለም::እርግ
ጥ ከ1966 በኋላ:ማህበሩ እንዲቀጥል ከተፈለገ: የግድ እ
ራሱን በገንዘብ በኩል በመቻል ከ ሃይለስላሴ ·የበላይ ተጠ
ባባቂነት· መውጣት እንደነበረበት ግልጽ ነው::ያልደሪያ
ጓዶች እዚህ ላይ ·ጥበቀ ዲሲፕሊን· የሚሉት ማህበርተኛው
ን የግድ እደር ማስከፈሉን ከሆነ ልክ ናቸው::በተለይ የ
ማህበሩ መኖሩ እራሱ ከጥያቄ ውስጥ በገባበት በዚያ
ወቀት የዚህን አይነት ·ዲሲፕሊን· ተገቢና ትክክለኛ ነ
ገር ነበር::ግን ጓዶቹ የሚሉት ·ዲሲፕሊን· የማህበሩን
አቀነባበርና/ስትራክቸር/ በመሪዎችና በማህበርተኞች መካ
ከል የነበረውን ግንኙነት የሚመለከት ከሆነ ፈጽሞ የሀሰት
ክስ ነው::ያልደሪያ ጓዶች ለምን ህገማህበሩን ወስደው
ከተነተኑ በኋላ የት ላይ ·ዲሞክራሲያዊ ሴንትራሊዝም·:
·ጥበቀ ዲሲፕሊን·. . . ወዘተ. እንዳለ አላመከቱም::
እንዲያውም ግለበበና/ሰበደበቲ/ በሆነ መንገድ የቀደምያ



ችን የማህበር መሪዎች ለማሳጣት ፈልገው ነው እንጂ:የማህ
በሩ አመራር ·ጥበቀ ዲሲፕሊንን· ከስራ ላይ ለማዋል ፈጸ
ሞ ምንም አይነት መሳሪያ ሲኖረው አይችል እንደነበረ —
አሁንም ሲኖረው እንደማይችል — ግልጽ ነው::ማህበሩ የፍ
ርድ ከሚሲዮን:ፖሊሲዊ ·ህግ አስከባሪና· በደረጃውና በ
ጥፋቱ የተዘረዘሩ መቀጫዎች አልነበሩትም::የሉትም::ሊኖሩ
ትም አይችሉም::

ምናልባት:ከዚህ በላይ በጠቀስነው የጓዶች አነጋገ
ር ውስጥ እንዲት የእውነት ቀንጣት ብትኖር ስለመሪዎች
ርእዮተአለም የሚናገሩት ነው::አንደኛ ነገር:ከዚህ በላ
ይ የጠቀስነው የፖለቲካ መስመር ለውጥ ራሱ እንዳችን የተ
ወሰነ የርእዮተአለም ዝንባሌ በሞላ ጎደል በማመልከቱ ግ
ማሹ ተማሪ ከማህበሩ እንዲሸሽ አድርጓል::ይህ ግልጽ ነው::
አልመለሰበትም::ግን:ሁለተኛ ነገር:የማህበርተኛው ቁጥር
እንደዚያ ከተቀነሰ በኋላ·በማህበሩ ውስጥ ከቀሩት ብዙዎቹ
ስለማርክሲዝም —ሌኒንዝም:ስለማኦ ትሴቱንግ ሀሳብ:ስለመደ
ቦች ትግል:ስለሳብአደሩ ሪቮሉሽን ... ወዘተ. በሰፊው
ማውራት ጀመሩ::ይህንን ለመረዳት ለመጀመሪያ ጊዜ በህዳ
ር 1967 የወጣውን ትግላችንንና የተከተሉትን ቦስተ—እ
ራት ቁጥሮች ይዞት ማስተዋል ይበቃል::ይህም:በኔ ግምት:
ያንዳንዶቹን ማሸገሸግ እንዳስከተለ አይጠረጠርም::

ይሁን እንጂ:ከ1968 መጨረሻ ወዲህ ያውሮፓው ማህ
በር የሚያወጣቸው መጽሄቶች በደፈናው:ባልተጨበጠ አኳኋን:
ስለመደቦች ትግልና ስለማርክሲዝም—ሌኒንዝም ቴወሪ በማውራ
ት ፈንታ የኢትዮጵያን የተጨበጡ ሁኔታዎች ለመመርመርና
በነርሱ ላይ በመመስረት እንባቢን ለማስተማር ሞከረዋል::

በዚህ በኩል፡ያለደሪያ ጉዶች ለማሸሟጠጥና ለማቀለል፡ለማሳጣት መሞከር — '. . . . አዲስ አይነት ዲሞከራሲያዊ መንግስት ይቋቋም በሚል አርእስት ከተጻፈ ሺህ የታጠቀ ጸሁፍ...'— እነዚህ መጽሄቶች በኢትዮጵያ ጭምር ያገኙትን ጥሩ ተቀባይነት ሊቀንሰው አይችልም፡፡ይልቁንስ ባሁኑ ጊዜ ይበልጥ ሊያሳስበን የሚገባው ባንዳንድ ጉዶች ዘንድ የሚታየው፡ያውሮፓው ማህበር በ1967 68 ወደነበረበት ደረጃ፡ወደኋላ፡የመመለስ ዝንባሌ ነው፡፡ይህ ዝንባሌ በተለይ፡ከዚህ ቦታ ባንዱ ቦታ በተጠቀሰው፡በስትራግል/ሰኔ 1971/ ላይ በደንብ ይታያል፡፡መጽሄቱ ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ያልተያያዘ፡ያልተጨበጡ/አብስትራክት/ ሀሳቦችን ይዟል፡፡ ይህ ብቻ አይደለም፡፡በጠቀሳሳው የተፈጠረውን ያስተሳሰብ ውዥንብር የሚያባየው አንዱ ጉዱ 'በተጨበጠ አኳኋን/አብጀክቲሊ/ የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ የሳብአደሩን ሚና/ሮል/ ለመቀማት ሞክሮአል'/ገጸ 54/ ብሎ ከከሰሰ በኋላ፡ቀጥሎ ደግሞ ይህው 'የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ የሳብአደር ፓርቲ እንዲያደራጁ'/ገጸ 5ይ/ መጠየቁ ነው፡፡በኔ አስተያየት፡ይህንን የወደኋላ መመለስ ዝንባሌ በንቃት መቋቋም ያስፈልጋል፡፡

ነገር ግን፡ወደአባሉ ቁጥር ብዛት እንመለስና ጉዶች ከዚህ በላይ የሚሉትን እናስተውል፡፡በነርሱ አስተያየት አንዱ ድርጅት 'ህዝባዊ' የሚባለው ያባሉቹ ቁጥር ብዙ ሲሆን ነው፡፡ምነው ጉዶች፡፡ምን ነካቸሁ፡፡የቀደሞዎቹን የማህበር መሪዎች በማንኛውም መንገድ ለማሳጣት ስትቻኩሉ የማርክሲዝም —ሌኒንዝማቸሁን ሀሁ ረሳቸሁት፡፡እንኳንስ እናንተ'ንጹህ ንጹህ ሪቮሉሽናዊያን' ቀር ታቸሁ፡ምንም የድርጅ



ትን ጥያቄ ፊደል የቆጠረ ሰው እንደሚያውቀው፡አንዱ ድርጅት 'ህዝባዊ' የሚባለው በአባሉቹ 'ብዛት' ሳይሆን፡በውስጡ የተለያዩ መደቦችና በመደብ ጥቅሞች ብዛት ነው፡፡ህዝባዊ ድርጅት ከፓርቲ የሚለየው በዚህ ነው፡፡እርግጥ የመደብ ብዛት የቁጥርንም ብዛት ያስከትላል፡፡ግን ያባል ቁጥር ያንዱ ድርጅት 'ህዝባዊነት' መመዘኛ አይደለም፡፡በማህበራችን ውስጥ ያለው 'ሁለቱ መቶ' አባል በሙሉ ያንዱ መደብ ህዝብ ነው፡፡ያንዱን መደብ ጥቅም ለመጠበቅ ይቆማል ካልተባለ፡ማህበሮቻችን ህዝባዊ ድርጅቶች መሆናቸው ፈጽሞ አይጠረጠርም፡፡

በነገራችን ላይ፡ያውሮፓው ማህበራችን ሺህ አባሎች ቢኖሩት፡ያሚሪካው ስስት ሺህ — ባሚሪካ ከ1970 ወዲህ ሁለት ሺህ ሳይሆን ከስስት ሺህ በላይ ወጣቶች አሉ ይበላል — ቢኖሩት በጣም ጥሩ ነገር ነበር፡፡ግን ማንም ሊገምተው እንደሚችለው፡ይህ ሊሆን የማይችል ነገር ነው፡፡ለዚህም ብዙ ምክንያቶች አሉ፡፡አንደኛ፡አሁን ያሉት ማህበራት ማቴሪያላዊ አቅም የተወሰነ ነው፡፡ስለዚህም መሳውን ተማሪ ለማንቀሳቀስ ስራ የፕሮፓጋንዳና የማደራጀት ተግባር ሊፈጸሙ አይችሉም፡፡ሁለተኛ፡ባገራችን ገሐድና የተጣራ ፕሮግራም ሪቮሉሽናዊ ፓርቲ ስለሌለ፡በደፈናው ያሁኑን የኢትዮጵያን ስርአት የሚቃወም እንኳን ቢሆን፡ብዙው ተማሪ ማህበራት ከምንም አያደርሱም የሚል እምነት ስላለው ማህበራትን ቸላ ይላቸዋል፡፡ይህንን ቸልተኝነት ለማሸነፍ የሚቻለው በሰፊ የፕሮፓጋንዳና የማደራጀት ስራ ነበር፡፡ግን ይህም የተወሰነ መሆኑ ተጠቅሷል፡፡ሶስተኛ፡ከዚህ ሁሉ ጋር የተያያዘ፡የማህበሮቻችን ጸረፊውዳልና ጸረኢምፔሪያሊስት አቋም በደፈ

ናው ይታወቅ እንጂ፡ከግለሰቡ አባል የሚጠይቃቸው ግዴታዎች
ገና በደንብ ለሁሉም አልታወቁም፡፡ማለት ሪቮሉሽናዊ አስተ
ሳሰብ ገና በደንብ ስር አልሰደደም፡፡ሌሎችም ምክንያቶች
ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡ለምሳሌ፡በየቦታው ተሰበጣጥሮ መኖር፡እያ
ንዳንዱ አካባቢ በተማሪው ላይ ያለው ማቴሪያሊዊና መንፈሳ
ዊ ተጽእኖ... ወዘተ.፡፡ከነዚህ ሁሉ ምክንያቶች የተነሳ
ተማሪውን ሙሉ በሙሉ የማህበሪት አባል ለማድረግ አይቻልም፡፡
ይሁን እንጂ፡ማህበሮቻችን ያባሎቻቸውን ቁጥር በየጊዜው
ከፍ ለማድረግ በመታገል መቀጠብ የለባቸውም፤እንዲያውም
የበለጠ ትጋትና ጥረት ማሳየት አለባቸው፡፡ዘጠና በመቶው
ን በአንድነት ለማሰለፍ የሚችሉበትን ዘዴ ለማግኘት ሁልጊ
ዜ መጣጣር አለባቸው፡፡

ያልጀሪያ ጓዶች እንዲህ ይላሉ፡–

"አብዛኛው ተማሪ በፖለቲካ ንቃተ ጸረፊውዳልና ጸ
ረኢምፔሪያሊስት ካልሆነ፡እውነተኛ ሪቮሉሽናዊ የ
ሆኑ ተማሪዎች ሪቮሉሽኑን የሚያገለግሉት ከአብዛኛ
ው ተማሪ ሸሽተው ጠባብ የምርጥ ሰዎች ክበብ በመ
ፍጠር ሳይሆን አብዛኛው ተማሪ ማህል ገብተው በመ
ታገል ነው፡፡ሁልጊዜ የማህበሩ አመራር በእኛ እጅ
መሆን አለበት በማለት ብቻ አብዛኛውን ተማሪ ማህ
በር ውስጥ ተካፋይ እንዳይሆን ማድረግ የለባቸውም፡፡
...ውጭ አገር ያሉ የኢትዮጵያን ተራማጅ ተማሪዎ
ች ትክክለኛ ርእዮተአለም በሰፊው ከማስፋፋት የተ
ሻለ ተግባር ሊሰሩ አይችሉም፡፡አገር ውስጥ ያለው
ማህበር ሁሉንም ተማሪዎች/የነርሱ ሰርዝ/ በማጠቃ
ለሉ ውጭ አገር ካሉት የበለጠ እንጂ ያነሰ የፖለ



ቲካና የርእዮተአለም ትግል አሳደረገም፡፡እንዲያውም
የህይወት መስዋእትነት ሳለበት ሪቮሉሽናዊ ትግሉ
በበንት ሺህ የሚቆጠሩ አባሎችን አሰልፍአል፡፡"/ገጽ
29-30.ሰርዝ የተጨመረ/

ደግሞም፡–

"... የማህበሮቻችን ዴሞክራታዊ አቋም አባሎችን ሁ
ሉ በውሳኔና ባመራር ተካፋይ እንዲሆኑ ሊያደርግ
የሚችል እንጂ አንዱ የተወሰነ ትንሽ ቡድን፡ወይም
የአንዱ ሁለት አገር ቀርንጫፍ ማህበሮች ብቻ ከአ
መት እስከአመት አመራሩን ካሳንዱ ተቆጣጣሪ በሞኖ
ፖል እንዲኝ በለው አንቀው እንዲይዙት የሚያስችል
መሆን የለበትም፡፡ሁለተኛ፡መሪዎቹ ግልጽ በሆነ
የዴሞክራሲያዊ ስነስርአት፡ቀጥታና ምስጢራዊ ድምጽ
አሰጣጥ የሚመረጡ መሆን አለባቸው፡፡ሶስተኛ፡በማህ
በሩ ውስጥ ማንኛውም አባል፡ማንኛውም ቡድን/ከአ
ብዛኛው የተለየ አስተሳሰብ ያላቸው በተለይ/ ሀ
ሳባቸውን ለመግለጽ ሙሉ ነጻነት እንዲኖራቸው ያ
ስፈልጋል፡፡..."/ገጽ 30-31. ሰርዝ የተጨመረ/

ያልጀሪያ ጓዶች እዚህም ላይ እውነቱን በማጣመም፡
እውነቱን ከውሸት ጋር በመደበላለቅ፡የተማሪ ማህበራትን
የቀደሞ አመራሮች በከንቱ ለማሳጣት ይሞክራሉ፡፡እዚህ ላ
ይ ለመስጠት የሚሞክሩት የማህበራችን ስእል ያንዳች ፋሽ
ስት ድርጅት መልክ አለው፡፡በተማሪ ማህበሮቻችን ውስጥ
የት ቦታ ነው "የምርጥ ሰዎች ክበብ" የተቋቋመው፡፡
የትና ማን ነው "አመራሩ በኛ እጅ ብቻ መሆን አለበት"

በሉ አብዛኛው ተዳሪ 'ተከፋይ' እንዳይሆን ያደረገው::አ
ንዱትስ አድርጉ ነው ይህንን ለማድረግ የቻለው:: የተጨበጡ
ሮቸና ምሳሌያች መስጠት ነበረባቸው::ሁኔታውን ዘርዝር
ማስቀመጥ ያስፈልግ ነበር::ግን የሀሰት ክስ ስለሆነ ጓደ
ቹ ይህንን አላደረጉም::

ያውሮፓው ማህበር አመራር በ1964 ጣሊያን:በ1965
አውስትሪያ:በ1966 እንግሊዝ:በ1967-68 ፈረንሳይ:
በ1969-70 ስዊድን:በ1971 ፈረንሳይ ነበር::እርግ
ጥ በነዚህ ባለፉት አራት አመታት ውስጥ በተለይ የፈረንሳ
ይና የስዊድን ማህበራት አመራሩን ተቀባብለዋል::ግን ይህ
የሆነበት ምክንያት ምንድን ነው::

ለዚህ ጥያቄ መልስ ለመስጠት ሁለት መሰረታዊ ነገሮ
ችን በደንብ ማስተዋል ያስፈልጋል::አንደኛው መሰረታዊ
ነገር የቅርንጫፍ ማህበራት/የያገሩ ማህበራት/ መጠንከርና
መዳከም የሚፈራረቅባቸው ድርጅቶች መሆናቸው ነው::በ1964
ያውሮፓውን ማህበር የመራው የጣሊያን ቅርንጫፍ ማህበር
ዛሬ ከናካቴው ጠፍቷል::እንዲሁም በ1965 የመራው የአው
ስትሪያ ውስጣዊ ማህበር::እንደዚሁም በ1966 በጓድ ሀ
ሩይ ተድላ ፕረዚዳንትነት ማህበሩን የመራው የእንግሊዝ ቅ
ርንጫፍ ዛሬ አለ ሊባል የማይችል ነው::በ1968 የማህ
በሩን ጉባኤ ያዘጋጀው ጠንካራ የቼኮዝሎቫኪያ ማህበር ዛሬ
በጣም ተዳክሟል::በ1966-67 ግድም በመጠኑም ቢሆን
በማህበሩ ኑሮ ይሳተፉ የነበሩት የግሪክ:የቡልጋሪያ:የሩ
ማኒያ:የቼኮዝሎቫኪያ:የእስፓኝ ማህበሮች ዛሬ ወይ ፈጽሞ
የሉም ወይንም በጣም የተዳከሙ ናቸው::ሁንጋሪያና ፖላንድ
ም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በሞትና በህይወት መካከል ተንጠል



ጥለው የሚኖሩ ማህበራት ናቸው::.... ከ1966 ወዲህ ያ
ለውን ሁኔታ በጠቅላላው ስንመለከተው:እየወደቀ እየተነሱም
ቢሆን መቀጠልን ያሳዩ ሰቪየትህብረት:ፈረንሳይና ስዊድና
ናቸው::ይህም ሊሆን የቻለው በነዚህ ማህበራት ውስጥ እ
ንዳጋጣሚ ረዘም ላለ ጊዜ አንዳንድ ተቀናቃኞች/ሚሊታንቶች/
ግለሰቦች ስለቆዩ የማያቋርጥ ትግል ስላደረጉ ነው::የ
ቀሩትም ማህበራት የጠፉት:ወይም የደከሙት ያውሮፓው ማህ
በር አመራር 'ኋምክራሲን' በማጥፋቱ ሳይሆን ቀድሞ የነ
በሩት ተቀናቃኞች ወዳገርቤት ወይም ወደሌላ ቦታ ስለተዛወ
ሩና ትግሉ ሊቀጥል ስላልቻለ መሆኑ ግልጽ ነው::የተቀናቃ
ኞች መጥፋት ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ችግሮች ላይ ሲደር
በ የዚህ አይነቱን ውጤት ማስገኘቱ ምንም ያህል አያስደ
ንቅም::

ሁለተኛው መሰረታዊ ነገር:ያውሮፓን ማህበር አመራ
ር በህገማህበሩ መሰረት የሚወስደው ያንድ አገር ቅርንጫፍ
ማህበር እንጂ ከያገሩ የተውጣጡ ግለሰቦች አለመሆናቸው
ነው::ያመራረጡም ዘዴ እንደሚታወቀው እንደሚከተለው ነው:-

በየጉባኤው መጨረሻ ላይ:የማህበሩን አመራር ለመው
ሰድ ፈቃደኛ የሆነ ማህበር እንዳለ ይጠየቃል::በመሰረቱ:
መጀመሪያውኑ ተዘጋጅቶ/ማለት የራሱን ማህበርተኞች ስምም
ነት አግኝቶ/ የመጣ ፈቃደኛ ማህበር እንዳለና ተወዳዳሪ
ከሌለው አመራሩ በጭብጨባ ይሰጠዋል::እኔ እስከማውቀው ድ
ረስ የዚህ አይነት ሁኔታ እስከዛሬ — በተለይም ከ1965ቱ
የፖለቲካ መስመር ለውጥ ወዲህ — በፍጹም ደርሶ አያውቅም::
ይህ የታወቀ ነገር ሆኖ ሳለ 'አመራሩ በኛ እጅ መሆን አ
ለበት' ያሉ/የሚሉ// አሉ ማለት:ወይንም ማንም በሙሉ ፈቃ

ደፕነት አመራሩን "እቀበላለሁ" ብሎ በማያውቀበት ቦታ
"ብዙ ሁኖ መጥቶ ከበልጣን እንዳያወርዳቸው" የፈራ ነበ
ር/እለ/ ብሎ መናገር በሀሰት መከሰስ ነው እንጂ ሌላ ት
ርጉም የለውም::ለመድገም ያህል:ከመጀመሪያው "እኔ ፈቃደኛ
ነኝ" ብሎ የቀረበ ማህበር አንድም አልነበረም::/አንዱ
ይህንን የሚያፈርስ የሚመስል አለ::ከዚህ በታች አነሳዋለ
ሁ::/ ፈቃደኛ ተጠይቆ ሲጠፋ:ከቤቱ ውስጥ ጥሪያቸ:የማህ
በር ሰዎች ይቀርባሉ/ኖሚኖት ይሆናሉ/:: የሁለት ሶስት
ማህበራት ስም ከቀረበ በኋላ:ጉባኤው ለትንሽ ጊዜ ቆም
ብሎ:የነዚህ ማህበራት ወኪሎች ሀላፊነቱን ለመውሰድ ይችሉ
እንደሆነ ለየብቻቸው ይመካከራሉ::ከዚህ በኋላ በርግጥ
ፈቃደኛ የመሰለው "ተለምኖ":"አይዘህ:አይዘህ" ተብሎ በ
ስንት ጣጣ ያመራሩን ሀላፊነት ይቀበላል::እስከዛሬ ደርሰ
አያውቅም እንጂ:እንዳጋጣሚ ሆኖ ብዙ ተወዳዳሪ ማህበራት
ፈቃደኛ ሆነው ከቀረቡ ጉባኤው በድምጽ ብልጫ አንዱን ^መ
ርጣል::

ከዚህ በላይ እንደተጠቀሰው — ያልጀሪያ ጓዶች አጣ
ምመው:ተንኮል አስመስለው ያቀርቡታል — ባለፉት አራት አ
መታት ውስጥ የሰዊድንና የፈረንሳይ ማህበራት ያውሮፓውን
ማህበር እየተቀባበሉ መርተዋል::የሶቪየት ህብረቱ ማህበ
ር በያመቱ እየተጠየቀ ባገሩና በመንግስቱ አስቸጋሪነት ም
ክንያት ሁልጊዜ እምቢ እንዳለ ነው::በዚህ ሁኔታ:እነዚህ
ሁለት ማህበሮች በያመቱ "እየተለመኑ" ሀላፊነቱን ለመቀ
በል ተገደዱ እንጂ:"ባላንዱ ተቀጣጣሪ በሞኖፖል እኝኝ
ብለው አንቀው" እንዳልያዙት ለማንም ሀቁ:በጥላቻ ሳል
ቱላ ሰው ገልጽ ይመስለናል::



ገገልጀሪያ ጓዶች ይህንን በመርዘኛ ጥላቻ የተሞላ
ክስ እንዲስነዝሩ የገፋፋቸው አንድ አጋጣሚ አለ::ይህውም
በ1971 በበርሊን በተደረገው አስራአንደኛ ጉባኤ ላይ
የደረሰው ነው::በዚህ ጉባኤ ላይ ሁለት:ለመጀመሪያ ጊዜ
በስብሰባ ላይ የተገኙ:ከቤኔሉክስ የመጡ ጓዶች — ከዚያ
ወዲህ በወስዷቸው አንዳንድ ጸረዲሞክራሲያዊና ጸረድርጅት
እርምጃዎች እስከመታወቅ የደረሱ ጓዶች — የማህበሩን አመ
ራር እንወስዳለን ብለው ተነሱ::ነገር ግን ሌሎችም ከቤኔ
ሉክስ የመጡ ጓዶች ስለነበሩ:ከነርሱ ውስጥ አንዱ:የቀር
ንጫፍ ማህበሩ ጸሀፊ የነበረው:ይህንን ያመራሩን ሀላፊነት
የመውሰድ ጉዳይ አስቀድሞ የቤኔሉክስ ማህበር:ለጉባኤው ባ
ይመጡ በፊት:ተነጋግሮበት እንደነበርና ማህበሩም ሀላፊነቱ
ን ከመውሰደ እንዲቆጠቡ ውሳኔ እድርጉ እንደነበረ አስታወ
ሰ::በዚህ ሁኔታ:ገና በውስጡ ስምምነት ያላገኘ ማህበር
አመራሩን ከመስጠት ልምዱ ያለውና ስምምነት ያለው ለሰዊዱ
ን ማህበር እንደገና መስጠቱን ጉባኤው ቢመርጥ ትክክለኛ
ነበር::

የመጸሄት ቦርዱንም አመራረጥ ብንወስድ ነገሩ ይህ
ንኑ የመሰለ ነው::መጀመሪያ ፈቃደኛ እንዳለ ይጠየቃል::ኖ
ረም አልኖረም ከቤቱ ውስጥም ሰዎች ይስነዘራሉ::ከእነዚህ
ሰዎች ውስጥ ከፍተኛውን የድምጽ ቁጥር ያገኙት የመጸሄት
ቦርድ አባሎች ይሆናሉ::/በነገራችን ላይ:በዚህ ባለፈው
12ኛ ጉባኤ ላይ:እላይ ከተጠቀሱት ሁለት የቤኔሉክስ ጓደ
ች አንዱ ለመጸሄት ቦርዱ አባልነት ከምርጫ ውስጥ ገብቶ
ነበር::የተመረጡት ጓዶች ከሰባ እስከሰማንያ ድምጽ ሲያገ
ኙ:እንደማስታውሰው ከሆነ:ይህኛው ጓድ ወደሰላሳ ገደም ድ

ምጽ በማገኘቱ ባይመረጥ ቀርቷል::ያልጀሪያ ጓዶች ጥላቻቸ
ውን ባመራሩ ላይ የሚያወርዱት በዚህም ምክንያት ይሆን እ
ንደሆነ አላውቅም::/

ይህ ያመራር ዘዴ ዴሞክራሲያዊ አይደለም:አይስማማ
ንም:ካሉ ያልጀሪያ ጓዶች ለውጥ እንዲደረግ ጉባኤውን ለመ
ጠየቅ መብት አላቸው::እንዲያውም በዚህ ጽሁፋቸው ውስጥ
ነገርን በማማታት የቀድሞ መሪያቸን ለማሳጣት በመሞከር
ፈገታ:አንድ—ሁለት—ሶስት ብለው በዝርዝር በማህበሩ ህገ
ማህበር ውስጥና በዘልማድም የሚደረጉትን አሰራሮች የመለወ
ጧ:የማሻሻያ ነጥቦች ለማቀረብ ይችሉ ነበር::ግን እውነቱ
ኖው የጽሁፋቸው አላማ ይህ ስላልሆነ ይህንን አላደረጉትም::
ምናልባት የለውጥ ነጥብ አቀርበዋል ቢባል 'ቀጥታና ምስጢ
ራዊ ድምጽ አሰጣጥ' የሚለው ሀሳብ ነው::

እስከዛሬ ድረስ በማህበራችን ውስጥ ማንኛውም አባል
የተስማውን:የሚያምነውን ለመናገር:ለመጻፍ:እንደታየው ለመ
ምረጥ መብት ነበረው::አለው::ያውሮፓው ማህበር አመራር
የወቀሱትን:የተቃወሙትን:'ከስልጣን' ያወረዱትን ግለሰቦች
ለመከታተል:ጧቆ ለመያዝ:ወይንም በነርሱ ላይ ጉዳት ለ
ማድረስ:ፈጽሞ እንዳችም ፖሊስ ወይም መሳሪያ የለውም::
በተጨማሪም 'ከስልጣን' ላይ የሚመጡት ጓዶች በየጊዜው
የሚለዋወጡ:በፈቃደኝነት የሚገቡበት ናቸው እንጂ:ማህበሩ
ወይ የግላቸውን:ወይንም የወገናቸውን የመደባቸው ጥቅም
የሚጠብቁበት መሳሪያ አይደለም::ስለዚህ:ድምጽ በሚሰጥበት
ጊዜ አባል ሁሉ ማንንም ሳይፈራ እጁን አንስቶ ለየትኛው
ምርጫ እንደሚቆም በግልጽ ያሳያል::ግን ይህ ያመራረጥ ዘ
ዴ ለግለሰቡ ማህበረተኛ አደጋ ሊያስከትል ይችላል ብለው



ያልጀሪያ ጓዶች ካመኑና ይበልጡን ማህበረተኛ ለማሳመን
ከቻሉ 'ቀጥታና ምስጢራዊ የድምጽ አሰጣጥ' ቢደረግ በበኩሌ
ግድ የለኝም::

ያልጀሪያ ጓዶች የማሳጣትና የማወናበድ ጉጉት ትንሽ
እንኳን ቆም ብለው አዙረው እንዳያጤኑ ያደርጋቸዋል::ማንም
ትንሽ አዙሮ የሚያስብ ሰው ያገርቤቱን የኢትዮጵያ ተማሪዎ
ች ማህበርና የውጭ ማህበራትን በአባሎች ቁጥርና በድርጊት
ለማመሳሰል አይቃጣም::ሁለቱን በነዚህ መለኪያዎች ለማነጻ
ጸር መሞከር ፍጹም ስህተት ነው::ባዲስአበባ ያሉት ተማሪ
ዎች ባንድ ቦታ የተሰበሰቡ:ባንድነት የሚኖሩ:ሁለቀን የሚ
ገናኙ ናቸው::በተጨማሪም የነርሱ የተጨበጡ ማቴሪያላዊ ሁ
ኔታዎች በውጭ ካሉት ፈጽሞ የተለየ ነው::በዚህ ሁኔታ:'ሁ
ሉንም ተማሪዎች' ማጠቃለልና ባንድነት ለማሰለፍ መቻል
ብዙ ችግር የለበትም::አስደናቂ ይሆን የነበረው በዛሬው
ሁኔታቸው 'ሁሉንም' ለማሰለፍ ባይችሉ ነበር::/በነገራች
ን ላይ:ይህ ለተማሪ ማህበር ብቻ ሳይሆን ለሰራተኛው መደ
ብም:ለገበሬውም እውነት ነው::ባንድነት ባንድ ቦታ የተ
ጠራቀመ የህዝብ ክፍል ለድርጅትና ለቀስቀሳ ይመቻል::/
በውጭ አገር ያሉት ማህበራት በብዙ መቶና በብዙ ሺህ ኪሎ
ሜትር ተራርቀው:በየቦታው ተሰበጣጥረው የሚኖሩትን ተማሪዎ
ች ለማደራጀት ይጣጣራሉ::ይህ ብቻ ሳይሆን:በነዚህ ተማሪ
ዎች ላይ የያንዳንዱ አገር ፖለቲካዊና ህብረተሰባዊ ተጽእ
ኖዎች የሚያደርሱትን ጸረድርጅት መንፈስ ማሸነፍ አለባቸው::
ሁለቱን ፈጽሞ ለማመሳሰል የማይቻለው በነዚህ ግልጽ ምክን
ያቶች ሲሆን:እንደዚያም ሆኖ:ባሉበት ሁኔታ:የውጭ ሀገር
ማህበሮች ያገርቤቱን በመደገፍ ከመስከብ እስከ ዋሽንግተን:

ከስቶክሆልም እስከፓሪስ በመቀነባበር የሃይለስላሴን መንግ
ስተ መደብሮች በጉልበት የያዙበት ወቅት እንደነበረ ማስታ
ወስ ያስፈልጋል::

አንዱ የመጨረሻ ነጥብ:ከ1966–67 ወዲህ ያውሮፓ
ው ማህበር ከጥንቱ:በሃይለስላሴ 'የበላይ ጠባቂነት' ስ
ር ይኖር ከነበረው ማህበር እጅግ በጣም ያነሱ አባሎች
ይኖሩት እንጂ:በፕሮፓጋንዳና በቅስቀሳ:ከማንኛውም ጊዜ
በልጦ ይገኛል::ከህዳር 1967 በፊት ከመቶ ጠቅላላ ጉባ
ኤ በስተቀር ምንም ስራ አልነበረም::ከዚያን ጊዜ ወዲህ
ማህበሮች ባሉበት ቦታ ሁሉ ጥናትና ቅስቀሳ ይደረጋል::ቢ
ያንስ በወር አንዴ ጊዜ መጽሄት ይወጣል::<u>ታጠቅና ትግላችን</u>
በጠቅላላው በውጭአገርና ባገርቤት አንባቢያች የሰጡት/የሚ
ሰጡት/ትምህርት በኔ ግምት ትልቅ አስተዋጽኦ ነው::ምናል
ባት እነዚህ መጽሄቶች ቀደም ባልደሪያ ጓዶችና በሌሎችም
ቸኳይና ግልፍተኛ <u>የንኡስቡርዧ ሪቮሉሽነሮች</u> ያሳደሩት አ
ስተያየት የውጭ ማህበሮቻችን የፖለቲካ ፓርቲዎች 'መሆናቸ
ውን' ይሆናል::ማህበሮች የተማሪ ድርጅቶች ብቻ መሆናቸው
ን ተገንዝበው ስለበሸቁ:እነዚህ ጓዶች እስካሁን በስንት
ጥረትና ትግል:በብዙ መስዋእትነት የተሰራውን ሁሉ ለማቀለ
ል:ለማሳጣትና ከንቱ ለማስመሰል መሞከር ፈጽሞ አይገባቸው
ም::እነዚህ ጓዶች በቀደም የማህበር አመራሮች ላይ የማባ
ጣት ዘመቻ በማድረግ ፈንታ አብረዋቸው በሃይለስላሴ መንግ
ስት ላይ ቢዘምቱ የበለጠ ለሪቮሉሽኑ እንደሚያገለግሉ አ
ይጠረጠርም::

ያውሮፓው ማህበር በነዚህ ባለፉት ጥቂት አመታት ው
ስጥ የማይናቅ ውጤት ያገኘው — ከዚህም የተነሳ አሁን



የከፋፋዮች ኢላማ የሆነው — በማህበሩ አመራር አንዳች አ
ይነት መቀጠል/ኮንቲኑዊቲ/ አንዳጋጣሚ ስለተገኘ መሆኑ አ
ይካድም::በኛ ማህበር ብቻ ሳይሆን በማንኛውም ድርጅት ው
ስጥ ያመራር መቀጠል:የማህበሩን ዲሞክራሲያዊ አቋምና አ
ቀነባበር እስካልተቃረነ ድረስ:ጥቅምን እንጂ ጉዳትን አያስ
ከትልም::በወሰንየለሽ ዲሞክራሲ/ኡልትራዲሞክራሲ/ በመገፋ
ፋት ብቻ:<u>ለመለወጥ ብቻ</u>: ተብሎ በያመቱ አዲስ አመራርን መ
ፍጠር ከሰዎች የስራ ልምድ ለማህበሩ እድገት ሊገኝ የሚች
ለውን ትርፍ ማስቀረት ብቻ ሳይሆን:ጸረድርጅት መሆንም
ነው::ያውሮፓው ማህበር ከቅርንጫፍ ማህበራት ነጻ የሆነ:
ቋሚ:ለሁለት ለሶስት አመታት በደመወዝ ተቀጥሮ የሚሰራ
የስራአስኪያጅ ኮሚቴ ለመፍጠር ያሰበበት ጊዜ እንደነበረ
አስታውሳለሁ::ሁኔታው ፈቅዶ ቢሞከር ኖሮ ከዚህም አዲስ
ትምህርትን ለማግኘት በተቻለ ነበር::

<u>መደምደሚያ — የተቀናበረ ዘመቻ</u>

የጥላሁን ታከለ ጸሁፍ የወጣው በማርች 1971 ቢሆ
ን:ያቀራረቡ ቀና አላማ ይህን ያህልም የብሄሮችን ጥያቄ
ለማብራራት ባይሆን — ይህ ቢሆን ፍጹም ሌላ በሆነ አቀራ
ረብ ይጻፍ ነበር — ይበልጡን የተጻፈው የተባሉትን ጓዶች
<u>ለመደምሰስ</u> እንደነበረ አይተናል::የተከሰሱት ጓዶች ከማህ
በሩ እንዲገለሉ የግድ ሆነባቸው::በዚሁ በ1971:ከጥላሁ
ን ታከለ ጸሁፍ በጥቂት ወራት ዘግይቶ ከሶሺየት ህብረት
ያውሮፓውን ማህበር አመራር በዚያው ቋንቋ የሚቃወም ጸሁፍ
ከነመልሱ በመጽሄት ወጥቷል::ለዚህ ጸሁፍ ምክንያት የነበ
ረው አመራሩ በከረን ጭፍጨፋ ላይ ያወጣው መግለጫ ነበር::
ከርሱ ጸሁፍ ቀጥሎ:ባለፈው አመት:ከቤኔሉክስ የ<u>ታጠቅን</u> አ

ገዱ ቁጥር ምክንያት በማድረግ በመጽሄት በሊዳትን ሳይ:
በዚያው በጥላሁን ታከለ ቋንቋ:ይህ ነው የማይባል የሀሰት
ክስ ቀርቦ ለርሱም እንደዚሁ መልስ ተሰጠው::ያልደሪያ ጋ
ዶች አሁን የሚያቀርቡት የሀሰት ክስ ከነዚያ የሚለየው እ
ንደምክንያት ጨማምር በሚወስዷቸው ነጥቦች ነው::በብሄራዊ
ጥያቄ:በታጠቀ ጸሁፍ:አሁን ደግሞ በተጨማሪ በማህበር 'ዲ
ሞክራሲ'... ወዘተ. አመካኝተው ከያቀጣጧው 'ጓዶች'
በተቋናበረ አሷኗን ባወርጀው ማህበር አመራር ሳይ — በተ
ለይም በቀደም መሪ ጓዶች ሳይ — ተለቀ ዘመቻ ይዘዋል::
ለዚህ ዘመቻ እንደጥሩ አጋጣሚ የተወሰዱት ልዩ ልዩ ምክን
ያቶች እንደሚያሳዩት:እነዚህ ጓዶች ገንቢ ስራ በመስራት
ፈንታ — እስካሁን አንድም የኢትዮጵያን ሪቮሉሽን የሚመለ
ከት ደገበና ጥናት አላቀረቡም — አደፍጠው የመንከሻ አዱ
ሰና የሚነከስ ሰው ይጠብቃሉ::በተከከለና የንኡስ ቡርዧ
ሪቮሉሽነኝነት/ሪቮሉሽኒዝም/ ግለትን:እንፍላሉትን/ኢከሳ
ይተሜንት/ ዱራማን:ሀይ—ሀይ የሚያስኘውን ሁሉ አጋጣሚ ለ
መፍጠር ይፍጨረጨራሉ::ግን የሚነከስ የግራከንፍ ወይም ዱ
ራማን የሚያስከትል አርእስት ሲያልቀባቸው ነገ እርስ በ
ርስ መነካከስን:መበጣጠቅን እንደሚጀምሩ ፈጽሞ አለጠራጠ
ርም::ለዚህ በምእራብ አውሮጀው የተፍለቀለቀት 'የግራ
ከንፍ' ዱንከ'ድርጅቶች' ምሳሌም ማስረጃም ናቸው::

እኔ እንደሚመስለኝ:ሪቮሉሽናዊ ተማሪያቸና ምሁራን
ሁሉ የነዚህን ከፋፋዮች ድርጊት ቸላ በማለት ፈንታ በደ
ንብ መቋቋም አለባቸው::ያለበለዚያ በንኡስቡርዧ ግልፍተኘ
ነታቸው የሚያከናውኑት ተንኮል የተማሪ ድርጅትን ብቻ ሳ
ይሆን ጠቅላላውን የኢትዮጵያ ግራከንፍ በመበታተን ለአደሃ



ሪው የኢትዮጵያ በርእስት ዋና አጋዥ ሁነው ይገኛሉ::

ያልደሪያን ጓዶች በሚመለከተው በኩል:ምንም እንኳ
ን ተለቀ ጥርጣሬ ቢኖረኝም:'መሳከቴን የጻፍሁት በንጹህና
በቀን መንፈስ:ከልብ የተሰማኝን:ልክ እንደተሰማኝ/ሳልሸ
ፋፍን/:በተጨማሪም በደንብ አስቤበት:ነውና ... በቀን
መንፈስና በሪቮሉሽናዊ ድፍረት እንዲቀበሉልኝ አጠይቃለሁ::'

በቀለ ወዳጄ

ታህሳስ 1965

## Resolution of the 6th Congress of NUEUS.

Addis Abeba, 1967

### Resolutin On Sectarian Movements In Ethiopia

Considering that there have been repeated attempts to raise sectarian movements in Ethiopia,

Considering that the reactionary Arab forces of the Middle East have shown keen interest in this agitation,

Considering that the petty bourgeois opportunists and reactionary elements have a vested interest in such sectarian movements,

Considering that the anti-national and reactionary forces would favour fanning it,

Considerig that the peneteation of such bourgeois and reactionary outlook would cripple the erection of a national democratic front,

Considering that these influences disturb and poison the genuine political education of the Ethioian people,

Considering that such sectarianism can be used by the imperialists to thier own advantage,

The 6th Annual Congress of NUEUS in its meeting in Addis Abeba(Ethiopia) from March 9,1967,

Condemns totaly the reactionary and sectarian movements in Ethiopia which the bourgeois and reactionary forces want to exploit,

Denounces the reactionary forces of the Middle East as accomplices of imperialism in exploiting the situation,

Condemns unconditionally the divisionists and factionalists sneaking into the ranks of the democratic organisations of the Ethiopian people,

Calls upon the democratic forces to be vigilant against the renegades and opportunists among the intellectuals that repeatedly succeed in deceiving the mass.

ዋጋው ፣ 1.50 ብር